## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ

## የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርስቲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርስቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የዲላ ዩኒቨርስቲ የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል የውስጥ ገቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡-
   1. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሣብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው በሚገልፀው መሰረት ለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በጀት ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የሰኔ ወር የባንክ እና ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ወደ ተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) ሙሉ ለሙሉ ያልተመዘገበ እና የባንክ ሂሳብ /የጥሬ ገንዘብ/ የሌጀር ሚዛን ያልታወቀ በመሆኑ፣
      - በኩልፎ ካምፓስ በገንዘብ ያገዥ እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ የሌለ ሲሆን በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታየው ብር 12,296.35 በመሆኑ በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረው በብር 12,296.35 የሚያንስ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
   2. የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡ የመምህራን የትርፍ

ሰዓት ክፍያ ፣የቤት አበል፣ በአካዳሚክ ዘርፍ በሃላፊነት ላይ ያሉ መምህራን የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች እንዲሁም በአስተዳደር ዘርፍ ስር ላሉ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈፀም፤

- በዋናው ግቢ የተሰበሰበው ብር 4,404,844.89፤ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተሰበሰበው ብር 5,695,592.05፤ በኩልፎ ካምፓስ የተሰበሰበው ብር 1,099,914.00፤ በነጭ ሳር ካምፓስ የተሰበሰበው ብር 4,027,893.03፤ በአባያ ካምፓስ ከመቀጠር ከሚገኘው ገቢ ግብር ከተሰበሰበው ብር 1,945,906.67፤ በጠቅላላው ብር 17,174,150.64 ከቅጥር የተገኘ ገቢ በሂሳብ መደብ 1101 መመዝገብ ሲኖርበት በሂሳብ መደብ 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች በሚል የተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከውጭ አገር ለጋሽ መንግስታት የሚያገኘውን የብድርና የእርዳታ ገንዘብ ከሚኒስትሩ በቻናል አንድ የገንዘብ ፍሰት የተላለፈውን፣ በመ/ቤቱ ባንክ ቀጥታ ከአበዳሪና እርዳታ ሰጪዎች የገባውን ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት የተዘጋጁትን ቻርት ኦፍ አካውንትስ፣ ቫውቸር፣ መዝገቦችና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን በመጠቀም ሂሳቡን መዝግቦ መያዝና ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት ከባንክ መግለጫው ጋር ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ ያገኘውን የፕሮጀክት ፈንድ

- ከDSS project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 390851 ብር 250,946 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 390852 የተሰበሰበው ብር 238,286፤ በድምሩ ብር 489,232.00፣
- ከSOLAR SAHAY Project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89502 ብር 500,000.00 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89505 ብር 500,000.00 በድምሩ ብር 1,000,000.00
- AEEP Project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 473299 ብር 146,289.00 ፣በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 473300 ብር 72,959.40 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89501 ብር 9,812.44 በድምሩ ብር 229,060.84፣
- ከNICH project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487906 ብር 215,242.20 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 488023 ብር 1,336,646.42 በድምሩ ብር 1,551,888.62፣

- ከSouth Design & Supervision በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487907 ብር 399,984.00፣
- ከSTICHTING IHE DELF በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487941 ብር 258,762.77፣
- ከRift Valley Lakes Basin Authority በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 488013 ብር 20,000.00፣

በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት ገቢው በገቢ አርዕስት ወጪውም በወጪ አርዕስት ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው፡ በተከፋይ ሂሳብ በዴቢትና በክሬዲት በማቀናነስ እየተመዘገበ መሆኑ፤

- ከVlir-ous Project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000155953946 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 1,271,513.25፣
- ከVlir-enset project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000134703311 እስከ ሰኔ 30/2008 ድረስ ብር 641,389.69፣
- ከNorhed Project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000021625918 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 433,467.22፣ በድምሩ ብር 2,346,370.16 የእርዳታ የገቢ ሂሳብ ዘመናዊ በሆነና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) የማይመዘገብ እንዲሁም የገቢ፤ የወጪ፣ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴ ምዝገባ፣ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት የማይመዘገብ፣ የሂሳብ ሪፖርት የማይዘጋጅለትና ለሚመለከተው አካል የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 4 ፊደል ሀ እና ለ የውስጥ ገቢን መጠቀም በማይቻልባቸው በመንግስት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንደ የተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን ለመሳሰሉት ወጪዎች የውስጥ ገቢን በመጠቀም መግዛት እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው

- በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 2,066,430.27 ለመደበኛና ለክረምት ተማሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የምግብ ግብዓቶች የውስጥ ገቢን በመጠቀም መግዛት በማይቻልበት ሁኔታ ከውስጥ ገቢ ወጪ ሆኖ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ዝርዝር ሁኔታው ከታች በአባሪ ቁጥር 1 ቀርቧል፡፡

5. በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 ክፍል ሁለት አንቀጽ 13 (መ) በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ለደመወዝ ሂሳብ ኦዲት በተወሰደ ናሙና መሠረት ለፊሊፒንስ፣ ለጀርመን ፣ለእንግሊዝ እና ለአዉስትራሊያ ዜጎች ከተከፈለዉ ብር 6,100,925.63 ደመወዝ ላይ ብር 1,970,315.76 የሥራ ግብር ተቀናሽ አለመደረጉ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል ፡፡

6. ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ማለትም እንጀራ ጋጋሪ፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት መስተንግዶና ጽዳት፣ ወጥ ቤት፣ እህል አበጣሪ፣ አትክልተኛ፣ ሁለገብ ጉልበት ሰራተኛ እና እንጨት ፈላጭ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በቀን ሰራተኝነት በመቅጠር በቀን ብር 22.90 በማሰብ

- በጫሞ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,211,479.65
- በኩፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 214,925.10
- በአባያ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,130,256.23
- በነጭ ሳር ካምፓስ በድምሩ ብር 622,516.50

በጠቅላላው ብር 3,179,177.48 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

7. ለትምህርት ወይም ሥልጠና በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱት ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው መመሪያው የተላለፈ ቢሆንም፣ በዩኒቨርስቲው የሰው ሃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት በቀረበው መረጃ መሰረት በኩልፎ ካምፓስ ለትምህርት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር የተላኩ ሠራተኛ መምህር ጨንቻ ጨቦ ከእንስሳት ሳይንስ የስራ ክፍል በቀን 20/12/2008 ወደ ውጭ የሄዱ ሲሆን ከመስከረም/2009 እስከ የካቲት/2009 ለ6 ወራት ያለአግባብ ሙሉ ደመወዛቸው ብር (6*10,470.00) 62,820.00 በመከፈሉ በድምሩ ብር **31,410.00** ከመመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል።

8. በአባያ እና በኩልፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 33,400.00 መምህራኑ ከዩኒቨርሲቲው ለቀው ሳለ ደመወዝ የተከፈላቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡
9. በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 17,667,845.32፣ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በድምሩ ብር 8,632,655.12፣ በጫሞ ካምፓስ በድምሩ ብር 7,368,645.17፣ በነጭ ሳር ካምፓስ በድምሩ ብር 1,645,104.50፣ በአባያ ካምፓስ በድምሩ ብር 4,344,919.73 እና በኩልፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,244,558.58 በጠቅላላው ብር **40,903,728.42** አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባ ተከፋፍለው በዋጋ ማቅረቢያ ብቻ የተገዙ መሆኑን

   በሁሉም ግቢዎች በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች ትክክለኛ የሆነ የገበያ ጥናት በማድረግ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ግዥው እየተፈጸመ አለመሆኑ፣ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
10. በዋና ግቢ በድምሩ ብር 1,006,884.30 ለዕቃ እና አገልግሎት ግዥ ያለውድድር በቀጥታ ግዥን መፈፀሙን፤
11. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 6 በአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ) መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈፀም ግዥ ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለግ እና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለመ/ቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ ከፊደል "ሀ እስከ ሰ" የተዘረዘሩትን አሰራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም እንደሚቻል በተገለፀው መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ በመመሪያው የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች በመከተል የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤
12. በዋናው ግቢ በተለያዩ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች እና የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 1,373,129.12፣ በመመሪያው የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎ በለቀማግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
13. ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት አመት ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ውል በመዋዋል የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ የፈጸመ ሲሆን፤ አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ዕቃዎችን ለዩኒቨርሲቲው ማስገባት ከነበረባቸው ቀናት ላሳለፉአቸው ቀናት በየቀኑ የውሉ 1/1000

ቅጣት፣ ከመሀቡብ ጀነራል ትሬዲንግ ብር 7,260.00፣ ከዶልቼ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 778,767.42፣ ከአይኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 910,516.17፣ ከጣሰው አንዳርጌ አጠቃላይ የጽህፈት መሳሪያ መሸጫ ብር 3,120.01፣ ከሰላም ሃዋሳ ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 13,745.94፣ ከአብይ ብርሃኑ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ብር 69,300.00፣ ከፍይን ኬሚካል ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 114,002.57፣ ከቴክ ፋይፍ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 3,058.88፣ ከኤምሂር ኢንጂነሪንግ ኢንተርፕራይዝ ብር 1,373,917.04፣ ከባዮቬት ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 76,185.07፣ ከእያሱ ጉልማ ብር 2,186.89፣ ከፐልስ ጠቅላላ ንግድ ድርጅት ብር 52,791.66፣ ከሪሊያብል የት/ት መሳሪያ አቅራቢ ብር 14,629.61፣ ከሶላሪስ ፓወርና አይሲቲ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 25,749.06 ከየትም ሱፐርማርኬት ብር 22,231.55 እና ከሀፌስ ሀሰን የህንጻ መሳሪያ ብር 12,629.40 በድምሩ ብር **3,480,091.25** የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

14. የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 16 ን.አ.16.14.2 ፊደል ለ) በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን እንዲሁም 16.14.4 በመንግስት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ሀ) የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን እንዳለበት ለ) በማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ተፈጻሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከ3 ወራት በኋላ ሊሆን እንደሚገባ ሐ) የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው ኤጀንሲው ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ መገለፅ እንደሚኖርበት መ) የመንግስት መ/ቤቱ በውሉ ላይ በተገለፀው እና በጨረታው መክፈቻ ዕለት ተፈጻሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ በኤጀንሲው ወይም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ

ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟላበት ሁኔታ በ2009 በጀት ዓመት ለ2008 ክረምትና 2009 የመደበኛ ተማሪዎች በማዕቀፍ በተፈጸመ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግልጽ ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ ከአርባ ምንጭ ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 24/05/09 በቁጥር 22-43/3/999 የወቅቱ የዋጋ ጥናት ዝርዝር በሚል የ11 ዓይነት ዕቃዎች የአንድ ወቅት ዋጋ ተጠይቆ ቀርቦ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ባለሙያዎች ተጠና ብለው ባቀረቡት የ13 ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ ጥናት በአምዩ አስተዳደር ካውንስል ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 22/2009 እንዲጸድቅ በማድረግ የዋጋ ማሻሻያ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት በድምሩ ብር **2,990,763.73** በብልጫ መከፈሉን ተረጋግጧል፡፡

16\. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ ኤጄንሲ ለ2008-2010 የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የተገባው ስምምነት ለዩኒቨርሲቲው በቁጥር 22;30/ግዥ/01/1168 በቀን 22/04/08 በላከው ውል ዝርዝር ላይ ያለ በመሆኑ ከአቅራቢዎቹ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- በዋናው ግቢ ከየትም ሱፐር ማርኬት የፕላስቲክ መጥረጊያ (plastic Broom) ብር 87,808.12፣በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከተለያዩ አቅራቢዎች የመጸዳጃ VIM 500gm እና የፕላስቲክ መጥረጊያ ግዥ ሲፈፀም በድምሩ ብር 67,250.00 በጠቅላላ ድምር ብር **155,058.12** በማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ከአቅራቢዎቹ መፈፀም ሲገባው በግልጽ ጨረታ እና በፐርፎርማ ግዥ በመፈጸሙ መንግስት ብር 155,058.12 ሊያጣ ችሏል::

15.በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ውሎች የሚዘጋጁት በቀረበው ጨረታ ሰነድ ላይ ባለው ዝርዝር ስምምነት መመሪያ (Specification) እንዲሁም ክፍያዎች የሚፈጸሙት በተገባው ውልና የዕቃዎች ዋጋ (bill of quantity) መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡- በዩኒቨርስቲው በዋናው ግቢ የሚገኘውን የጋራዥ ዙሪያ አጥር የግንባታ ስራ ለማሰራት በወጣ የአካባቢ ጨረታ ይበልጣል ኮንስትራክሽን ማህበር በቀን 05/12/2008 በቁጥር አምዩ4/7/130 አሸናፊ መሆኑ ተገልጾ ውል የተገባ ሲሆን ሆኖም ግን ውሉ በቀን 16 ህዳር 2008 በቁጥር አምዩ5/6/65 በይዞታ ልማት መ/መ/ዳ/ጽ/ቤት በቀረበው ስፔስፊኬሽኑ (Specification and bill of quantity) ላይ እንደተጠቀሰው ቆርቆሮ በሳይት እንደሚገኝ ወይም በዩኒቨርስቲው እንደሚቀርብና

የቆርቆሮ ዋጋ ብር 112,700.00 ከነቫቱ ወጪ እንደማይካተት (corrugated iron sheet 28 guage available at site, hence their costs are excluded) በተገለፀው መሰረት ሳይሆን የጋራዥ ዙሪያ አጥር ሙሉ ለሙሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ለመገንባት በሚል ውል ተገብቶ ከዚህ በታች በቀረቡት የወጪ ማስመስከሪያዎች የቆርቆሮን ዋጋ በማካተት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡-

16. የወጪ ሂሳቦች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት በሕጋዊ የክፍያ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ስናከናውን፣ ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13404 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54993 ብር 333,210.95 ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13406 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54963 ብር 45,489.42 ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13405 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 91480 ብር 84,284.19 በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቀርቦ የተወራረደ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለእነዚሁ አገልግሎት በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ መገኘቱን፣ በድምሩ ብር **462,984.56** በአንድ በተመሳሳይ ሰነድ ሁለት ጊዜ አለአግባብ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡

17. በዋና ግቢ በድምሩ ብር **74,626,574.31** የተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ትክክለኛውን የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ያልተመዘገቡ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

18. በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 3,091,874.79 ለ2008 በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥና ለዋለ አገልግሎት በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

19. በዋናው ግቢ በድምሩ ብር **4,493,020.81** ለዕቃና ለአገልግሎት ግዥ በተፈፀመ ክፍያ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

20. ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊትም ሆነ ቀድመው ለተከፈሉ ክፍያዎች ከመወራረዳቸው በፊት በቂ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ በናሙና ከተመረጡት ክፍያዎች እና ማስተካከያዎች ውስጥ በጠቅላላ ድምር **3,066,428.88** በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡

21. በድምሩ ብር 292,692.00 ከኃይለ ጊዮርጊስ እርገጤ የመፅሔትና የጋዜጦች መሸጫ መደብር የህትመት ግዥ እና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 55556 ብር 57,500.00

ከሳምኬት ኃ/የተ/የግ/ማ የቁልፍ መያዣ ግዥ በአጠቃላይ ድምር ብር 350,192.00 ክፍያ ሲፈፅም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተያየዘ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል :

22.በ2009 በጀት ዓመት በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ኮሌጆችና ዲፓርትመንቶች የካፌ ተጠቃሚና ተጠቃሚ ያልሆኑ ተመሪዎች ዝርዝር ለተማሪዎች አገልግሎት ተጠይቆ በቁጥር SSC/42/582/10 በቀን 25/03/10 በቀረበው መረጃ መሰረት የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የህዳር፣ የታህሳስ እና የየካቲት ወራት 2009 በልዩነት ብዛት በቁጥር 409 ተማሪዎች በብልጫ ብር **179,657.00** ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

23.በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ በናሙና ከተመረጡት ክፍያዎች ውስጥ በድምሩ ብር **715,907.86** ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ ምዝገባ ሳይከናወን መገኘቱ ተረጋግጧል ፡፡

24.ፍሊንት ስቶን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.ግል.ማህበር በአባያ ካምፓስ የኮንፈረንስ አዳራሽ፣ ፋውንቴን እና የሳይት ስራ አማካሪው አስልቶ ያቀረበው የቅጣት ብር መጠን ብር **15,677,585.83** ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከስሌቱ እና ከውሳኔው በኋላ ተሰርተው ከቀረቡ የሥራ ተቋራጩ ክፍያ ላይ **6,304,647.74 + 1,252,258.13 = 7,556,905.87** ተቆርጦ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 8,120,679.96የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

25.በቀን 29/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0705120 ከጀመአ እንጨትና ብረታ ብረት ስራ ማህበር በአባያ ካምፓስ ለተገነባው እስታዲዮም የመግቢያ በሮች ለማሰራት በክፍያ ማዘዣ ደብዳቤ ላይ እንዲሁም በድርጅቶቹ የገንዘብ መቀቢያ ደረሰኝ ላይ 30 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፊያ ብር 64,396.29 ሲከፈል በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መመዝገብ ሲኖርበት በወጪ የሂሳብ መደብ 6244 የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

26.ግብር ከፋዮች ከሚፈጽሙት ማናቸውም ክፍያ ላይ ሁለት በመቶ (2%) የንግድ ትርፍ ግብር (withholding Tax) ቀንሰው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው የተደነገገ ቢሆንም በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች ከተለያዩ ህንጻ ስራ ተቋራጮች በድምሩ ብር 3,178,253.56 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ቀሪ ማድረግ ሲገባው ብር

2,386,805.05 ተቀናሽ በመደረጉ በልዩነት ብር **791,448.51** ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ያልተቀነስ ዊዝሆልዲንግ ታክስ(2%) መገኘቱ

27. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ ፡በጠቅላላ በድምሩ ብር **23,008,110.11** በወቅቱ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

28. ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡- ከ2008 ጀምሮ በጠቅላላ ድምር ብር 1,915,612.36 የተለያዩ የአቅራቢዎች የመያዣ ሂሳብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 1001 ብር 262,228.60 ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች በሚል የተመዘገበ እና የመያዣ ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ መሆኑ

29. ዩኒቨርሲቲው በሂሳብ መደብ **5054**/ሌሎች የሚያዥያ ሂሳቦች/ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0001 ብር **300,751.16** ልዩ ልዩ ከመደበኛ ሂሳብ ተከፋይ እንዲሁም ብር **18,185,592.49** ልዩ ልዩ ከውስጥ ሂሳብ ተከፋይ በሚል በድምሩ ብር **18,486,343.65**፣ ለማን እንደሚከፍል በዝርዝር የማይታወቅና የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሠነድ ያልቀረበ በመሆኑ ሂሳቡን ለማጣራት ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

30. ለመደበኛ በጀት ከተደለደለው ውስጥ ለምግብ አገልግሎት ብር 9,014,538.64 ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 30 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የዩኒቨርስቲው የሂሣብ መግለጫዎች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ፣ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

**ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)**

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

- በድምሩ ብር **3,206,776.65** የመኪና መለዋወጫ እቃ ገዝቶ ሲቀይር የተቀየረው አሮጌ የመለዋወጫ እቃ ወደ ዩኒቨርስቲው ንብረት ክፍል ገቢ ለመደረጉ የአሮጌ እቃ ገቢ ደረሰኝ ከወጪ ሰነዱ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡
- በቀን 29/07/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0705175 ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ አገልግሎት ግዥ ብር 216,287.47 ለኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ ደቡብ ሪጅን በአባያ ካምፓስ በቀን 14/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ በድምሩ ብር **265,893.47** ከባንክ የወጪ ማስመስከሪያው ጋር የተያያዘው የክፍያ ማስረጃ ኮፒ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡
- መደበኛ በጀት በድምሩ ብር 13,895,825.27 በፐርሰንት 21.59% ተራፊ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡ለካፒታል በጀት ከተደለደለው ውስጥ  በድምሩ ብር 70,836,808.84 በፐርሰንት 39.35% ተራፊ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡ከውስጥ ገቢ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ በድምሩ ብር 17,182,425.72 በፐርሰንት 48.77% ተራፊ በጀት መገኘቱ

**ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)**

የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

- ብዛት ያላቸው መወገድ ያለባቸው የተለያዩ ዕቃዎች ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ኮምፒዩተር ግላሶች ፣ የፎቶ ኮፒ ቶነሮች ፣ የኮንቴንስ ወረቀቶች ፍሎፒ ዲስክ ሆንደር እንዲሁም የርቀት ትምህርት የማስተማሪያ መጽሐፍት መሳሰሉት ለበርካታ አመታት ሳይወገዱ በስቶር ውስጥ ከአዳዲስ አላቂ እቃዎች ጋር በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ዋና ግቢ  ቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣
  - ቢንካርዶች ከንብረቶቹ ጋር ተያይዞ የማይገኝና ወቅታዊ ምዝገባ ሳይደረግ ለብዙ ቀናት የሚቆዩ መሆኑን፤
  - የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያየ ብራንድ ያላቸው ቴሌቪዥኖች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ስታብላይዘር፣ ወንበሮች፣ ፍሪጆች፣ ፋክስ ማሽኖች፣ ስቶቮች፣ ፕሪንተሮች፣ ኮምፒዩተሮች እና UPS ምንም የሚወገዱ በሚል የተያዙ ቢሆንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው  ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣

- በ2009 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረት ቆጠራ ቢደረግም ቆጠራው የተደረገው በንብረት ክፍል ውስጥ ያሉትን ቋሚ እቃዎች ብቻ እንጂ በሰራተኞች እጅ ያለው እቃ ያልተቆጠረ መሆኑ፣

- <u>የኮንስትራክሽን እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣</u>
    - ከተገዙ ብዙ ጊዜ የሆናቸውየሻወር /የመታጠቢያ/ ቤት ሳህኖች ዩኒቨርስቲው ከሚያስገነባቸው ህንጻዎች ጋር የማይገጥሙ በመሆናቸው በሚል ያለመፍትሄ ተከማችተው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
    - ቴብል ፋን (የጠረጴዛ ቬንቲሌተር) ካርቶን አዳዲስና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸውን ለመቁጠር ያልተቻለ ለብዙ ጊዜ የቆየ ምቹ ባልሆነና ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ የተቀመጡ መኖሩን፣ እንዲሁም ቶርኖ እና ከ1980 ጀምሮ ገባ የተባለ የውሃ ማሞቂያ ቦይለር በቁጥር 9 በመጋዘን ውስጥ አለአግባብ የሚገኙ መሆኑን፤
    - በሞዴል ወጪ ተደርገዋል በሚል ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ የሌላቸው የዕቃ ማጠቢያ ሸቦ፣ የቀለም መቀቢያ ብሩሽ በካርቶን(5*120) 600, የቢሮ ቁልፍ ሙሉ ሲሊንደር ብዛት 250፣ ቆርቆሮዎች ብዛት 268፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና ሌሎችም ይገኛሉ

<u>የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ እቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- በመኪና መለዋወጫ ስቶር ውስጥ አዲስና አሮጌ እቃዎች አብረው መቀመጣቸው፣
- በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የመኪና መለዋወጫ ያልሆኑ ለረጅም ዓመታት የቆዩ ስማቸው የማይታወቅ እንደታሸጉ የተቀመጡ ብዛት 12 ማሽኖች፣ ዱፕሊኬቲንግ 23 ካርቶን፣ ዋይት ስቴንሲልስ እና ሌሎች እንዲሁም ጎማዎች ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣
- የተለያዩ ዓይነት የመኪና ባትሪ ባንድ ቢን ካርድ የተመዘገበ መሆኑን

<u>በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አላቂ ዕቃዎችን በሚመለከት</u>

- በሞዴል ወጪ ተደርገው በመጋዘን የሚገኙ ወረቀት በደስጣ 390,
- ማሽኖቻቸው የሌለ አገልግሎት የማይሰጡ ቀለሞች ብዛት ናኖዳስ 410 ቀለም,

<u>የቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከት</u>

- በሞዴል ወጪ ተደርገው በመጋዘን የሚገኙ ሚጋ ቀለም 28 ጋሎን መኖሩን፣

- በንብረት መጋዘን ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ወተር ቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት ለፊልድ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ታጣፊ ድንኳኖች እና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ዕቃዎች ለረጅም ዓመታት በመጋዘን ውስጥ እንደሚገኙ፣
- ቬንትሌተር (Desk Fam) አገልግሎት የሚሰጡ ቢንካርድ የሌላቸው ብዛት 38 ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን፣
- የተበላሹ ሜጋ ቀለሞች ብዛት 30 የሚገኙ መሆኑን፣
- ቢንካርድ ወቅታዊ የማድረግ ችግር መኖሩን

<u>በኩልፎ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፤
- ንብረቶች ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ በተዘበራረቀ ሁኔታ ለአቀማመጥ ምቹ ባልሆነበትና አቧራማ በሆነበት ሁኔታ ንብረቶች ተቀምጠው መገኘታቸው
- የተለያዩ ዕቃዎች ቢንካርዶች ወቅታዊ ምዝገባ አልተደረገባቸውም
- ፕሮጀክተሮች፣ ጄኔሬተር፣ የጨረጴዛ ቬንትሌተር፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ የፕሪንተር ቀለሞች ኮምፒተሮች፣ ፎቶ ኮፒ፣ የማባዣ ቀለሞች እና ሌሎችም ተመላሽ የተደረጉ አሮጌ ዕቃዎች አገልግሎት ከሚሰጡ ንብረቶች ጋር አንድ ላይ መቀመጣቸው፡፡

<u>ነጭ ሣር ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፣
- ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቆጠራ በፊት ንብረቶቹ በፊሰስ ሪፖርት ላለማቅረብ ንብረቱ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ወጪ የተደረጉ የጽዳት ዕቃዎች(መወልወያ ብዛት 380, የልብስ ሳሙና 2,683, ቪም 1475, ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተለያዩ ዓይነት የፕላስቲክ መጥረጊያና የዘንባባ መጥረጊያ) የኮንስትራክሽን ዕቃዎች(ሚስማር የተለያየ ሳይዝ በካርቶን 100, ሰርኩዩት ብሬከር ብዛት 22 በካርቶን፣ ፊውስ ብዛት በካርቶን 97, እና የፕሪንተር ወረቀቶች በደስጣ 1334) በሞዴል ወጪ እንዲያደርጉ ተደርጎ በቢንካርድ ላይ ወጪ ወይም ባዶ በማድረግ ንብረትን ለቁጥጥርና ለብክነት በሚዳርግ መልኩ የሚገኙ መሆኑን፡፡

- በመጋዘኑ ውስጥ ከቃጠሎ የተረፉ አገልግሎት የሚሰጡ HP A.L steincel printer፣ HOT Air Oven , የማብሰያ ዕቃዎች፣ የህክምና የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ ቴሌቪዥን፣ ዲኮደር፣ የማስተማሪ ዕቃዎች፣ እንዲሁም አሮጌ መጋዘን ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑን እና በአያያዝና በአቀማመጥ ለብልሽት ሊዳረግ በሚችልበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን
- የተለያዩ አገልግሎት ሰጥተው ተመላሽ የተደረጉ ኮምፒውተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ በንበሮች፣ የፕሪንተር ቀለሞችና የመሳሰሉት በመጋዘን ውስጥ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ መገኘታቸው

<u>በጫሞ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፣
- ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቆጠራ በፊት ንብረቱ በመጋዘን ውስጥ እያለ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች የተለያዩ ዓይነት የኮንስትራክሽን፣ የቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ እና የጽዳት ዕቃዎች ከነዚህም ውስጥ የመንገድ ላይ መብራቶች(Street lighting luminaire) ብዛት 30, የኤሌክትሪክ ሽቦ 2.5ሚሚ ባለ100 ሜትር ብዛት 21, ኤሌክትሪክል ቱል ኪት እሽግ ብዛት 8, ፍሎረሰንት ኦልደር 36እና ባለ18 ዋት ብዛት 125, ድሪል ማሽን ጅክሰን ማሽን ብዛት 5, ዊልዲንግ ማሽን ብዛት 1, ቬንትሌተር ብዛት 10, የጋውን ጨርቅ በሜትር 794, ሳይፎን ፍሌክሰቪል 833, የተለያየ ሳይዝ ወረቀት ብዛት ያለው፣ ኤር ፍሬሽነር 3,355, የሽንት ቤት መርዝ 1,288, ሮች ኪለር 2,137, የኤሌክትሪክ ኬብል 120ሜ, ድል ቀለም ብዛት 276, የሆቴል ማናጅመንት ብዛታቸው የማይታወቅ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች, ፕሪንተሮች 22, ኤልሲዲ 6, የቆሻሻ ማስቀመጫ ባልዲ ብዛት 50 እና የተለያዩ ዕቃዎች በሞዴል ወጪ እንዲያደርጉ ተደርጎ በቢንካርድ እና በስቶክ ካርድ ላይ ወጪ ወይም ባዶ በማድረግ ንብረትን ለቁጥጥርና ለብክነት በሚዳርግ መልኩ በፎርም የሚወጣ በሚል በንብረት መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፡፡
- የተለያዩ ተመላሽ የተደረጉ ላፕቶፖች, ፕሮጀክተሮች እና ሌሎች ዕቃዎች በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፡፡

<u>በአባያ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- መወገድ ያለባቸው የተበላሸ ብዛት ከ100 ኩንታል በላይ ጤፍ ከቋሚና አላቂ ዕቃዎች ጋር በመጋዘን ውስጥ የሚገኝ እንዲሁም ሌሎች ተመላሽ የተደረጉ፣

ያገለገሉ ወንበሮች ፣ የመምህራን አልጋዎች ባለ 1.20ሜ ብዛት 112፣ ችፑድ 1.50ሜ ብዛት የማይታወቅ፣ ኮምፒውተሮች፣ ቤድ ሳይድ ካቢኔት ብዛት 430, ፎቶ ኮፒ, ላፕቶፖች, ፕሮጀክተሮች, ቴብል ያልተገጠመ ድሮዎር፣

- እንዲሁም ቢንካርድ ሆነ ስቶክ ካርድ የሌለው የቧንቧ ዕቃዎች ብዛት ያላቸው፣ የጠረጴዛ ተገጣጣሚ ዕቃዎች ስፒከር እና ስፒከር ስታንድ ሞንታርቦ፣ Galileo scope ብዛት 3 በ2006 በእርዳታ ገባ የተባለ፣ free standing cooker አዲስ ቢሆንም አይሰራም የተባለ መኖሩን፣
- ብዛት ያላቸው የቢሮ ዕቃዎች በሙሉ በሞ/22 ወጪ ያደረጋቸው መሆኑን ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቆጠራ በፊት ንብረቱ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ወጪ ተደርጓል ይህም የተለያዩ ዓይነት የኮንስትራክሽን፣ የቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ እና የጽዳት ዕቃዎች ከነዚህም ውስጥ ሻወር ጌት ቫልቭ የተለያየ ሳይዝ ብዛት 190, Upvc የተለያየ ሳይዝ ብዛት 85, ሲሚንቶ ብዛት 100 ኩንታል, ቱቦላሬ ብዛት 550, (ሮች ኪለር ብዛት 1,980., ኤርፍሬሽነር 721, ሶላር ሳሙና 903, አጃክስ 1095, ኦሞ 530, የእጅ ጓንት ብዛት 40, እስፖንጅ 891, መወልወያ 1304, የፕላስቲክ መጥረጊያ 1016, ጋውን 600ሜ, ፎቶ ኮፒ ወረቀት 3850, ማበጥ ወረቀት 1000, ኡሁ 1670,) የሚገኝ መሆኑን፣

በአጠቃላይ በሁሉም ካምፓሶች የኩልፎ ካምፓስ በስተቀር ትልልቅ መጋዘኖች ያላቸው ቢሆንም በአግባቡ ጥቅም ላይ የማዋል ችግር መኖሩ ንብረቶች በየቦታው ተዝረክርከው እንደሚገኙ ንብረቶች በአይነት ለያይቶ የማስቀመጥ ችግር መኖሩን ሼልፎች በተሟላ መልኩ በመጋዘን ውስጥ የማይገኙ መሆኑን የጽዳት ችግር ያለባቸው እና በአቧራ የተሞሉ መሆኑን እንዲሁም ከፍተኛ ብዛት ያላቸው የኮንስትራክሽን የቧንቧ የኤሌክትሪክና የጽዳት ዕቃዎች በመጋዘን ውስጥ እያሉ በአንድ ላይ ወጪ በሞ/22 በማድረግ ቢንካርድና ስቶክ ካርድ ባዶ ማድረግና በተለያዩ ህጋዊ ባልሆነ ፎርም ወጪ ማድረግ በካማፓሶች የታዩ ችግር ሆነው ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው የንብረት ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም በእጅ እና በቢሮ በአገልግሎት ላይ የሚገኙ ንብረቶች ቆጠራ አለመከናወኑ፣ በተጨማሪ የተለያዩ የተጠናቀቁ ጊዜያዊ እና የመጨረሻ ርክክብ የተደረገባቸው ግንባታዎች ዩኒቨርስቲው ንብረት ለመሆናቸው በሚረጋገጥበት ሁኔታ በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ በተጨማሪም በቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ /Fixed Asset Registrationcard FAR/ እና

በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (Fixed Asset with user Control Card -UC) ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>የምግብ ጥሬ እቃ እና መድሃኒትን አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ</u> ፣

- በየካምፓሱ ያሉ የምግብ ጥሬ እቃ ሚኒ ስቶር ላይ የሚገቡ የምግብ ጥሬ እቃዎች ገቢ ሲሆኑ እንዲሁም ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሲወጡ በየቀኑ የተጠናከረ የምዝገባ ስርዓት ስለሌለ ከወጪ ቀሪ መኖሩና አለመኖሩን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ለአገልግሎት እንዲውል ገቢ የተደረጉ 7 ኮምፒውተሮች በምግብ ቤት ስቶር መቀመጣቸውና ሲወጡም በሞዴል ወጪ የማይደረጉ መሆኑን
- ዋናው ግቢ የሚገኘው ዲስፐንሰሪ ሞዴሎችም ሆነ ቢንካርድ የማይጠቀሙ መሆኑን፣
- ከዋናው ግቢ የተማሪዎች ክኒሊክ በስተቀር በሁሉም ካምፓሶች መድሃኒት ስርጭት/እደላ/ ክፍል የመደኃኒት ቆጠራ ያልተደረገ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምን ያህል መድሃኒት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፣ እንዲሁም ለዲስፐንሰሪ መድኃኒት ወጪ ሲያድርጉና ከዋናው ግቢ የመድኃኒት መጋዘን መድኃኒት ሲረከቡ ሞዴሎችን የማይጠቀሙ መሆኑን፣
- መድኃኒት ለተጠቃሚው የሚታደልበት ፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ተከታታይ ቁጥር የሌለ በመሆኑ ወጪ የሆነውን መድሃኒት በትክክል ለማወቅ የማይቻል መሆኑን፣ የተበላሹ መድኃኒቶች በመድኃኒት መጋዘን ውስጥ የሚገኙና በወቅቱ የማይወገዱ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

**በዋናው ግቢ አላቂ እቃዎች በተመለከተ**

- ቶነሮችን በዩኒቨርሲቲው ደረጃ ማስወረድ የማይቻልና እንደ አገርም የተወሰነ ውጣኔ ባለመኖሩ የተነሳ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የላከ ሲሆን ስለአወጋገድ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገ/ት ለግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ምላሽ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን፡፡
- በዩኒቨርሲቲው በዋናው ገቢና በካምፓሶች የሚገኘ ብዛታቸው 1655 የሆኑ የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮችና ስታብላይዘር፣ ኮፒ ማሽኞችና ታይሪራይተሮች እና ሌሎች ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ለኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስተር የኮሚፒተር ማደራጃና ማሰልጠኛ ማዕከል አስረክበናል፡፡ /4 ገጽ መረጃ ተያይዟዋል/ ቀሪዎች የተበላሹና አገ/ት የማይሰጡ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን አሰባስበን በማዕከሉ ለማቅረብ እየሰራን እንገኛለን፡፡

የፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም ኦዲት ሲከናወን፣

- የሠሌዳ ቁጥራቸው ኢ.ት 4-17648 ሚኒባስ እና ኢ.ት 4-21823 ኮስተር ባስ ሊብሬ የሌላቸው መሆኑ በተጨማሪም ደህ 5 - 0327 ያማሃ ሞተር ሳይክል_ የፌዴራል መንግስት የሰሌዳ ቁጥር ሊኖረው ሲገባ የደቡብ ብሔርና ብሔረሰቦች የተሽከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር የተሰጠው መሆኑን ፤
- የሰሌዳ ቁጥራቸው ኢ.ት 4-01258 ካቻማሌ አውቶብስ ፤ኢ.ት 4-01261 ካቻማሌ አውቶብስ፣ ኢ.ት 4-13408 ዳዎ አውቶብስ፣ ኢ.ት 4-14569 መርቼዲስ አውቶብስ፣ ኢ.ት 4-13417 ኮስተር ባስ፣ ኢ.ት 4-13412 ኒሳን ፒክአፕ፣ ኢ.ት 4-09338 ቶዮታ ሃይሉክስ፣ ኢ.ት 4-11511 ቶዮታ ሃይሉክስ፣ ኢ.ት 4-01266 ቶዮታ ስቴሽን ዋገን፣ ኢ.ት 4-13402 ቶዮታ ላንድክሩዘር፣ ኢ.ት 4-09342 ኤኔትሬ፣ ኢ.ት 4-11473 ፊያት110፣ ኢ.ት 4-23713 ቶዮታ ቴሽን ዋገን ኢ.ት 4-6818 ሞተር ሳይክል እና ደህ 5-0327 ያማሃ ሞተር ሳይክል ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የማይሰራ መሆኑና ተሽከርካሪዎቹ በሄዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

## 5.1. <u>የጄነሬተር ነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ፣</u>

- በዋናው ግቢ 5፣ በኩልፎ ከአምፓስ 1፣ በአባያ ካምፓስ 2፣ በጫሞ ካምፓስ 2 እና በነጭ ሳር ካምፓስ 1 ለሚገኙ ጀኔሬተሮች የነዳጅ ፍጆታ ሲዳሰስ ጀኔሬተሮቹን ለማንቀሳቀስ በሰዓት ወይም በቀን የሚያስፈልገው የነዳጅ መጠን ጥናት ያልተደረገና መጠኑ ያልተወሰነ በመሆኑ የመቆጣጠሪያ ስልት የሌለ መሆኑ፣
- ለጀኔሬተሮቹ የዋለውን የነዳጅ ፍጆታ ብዛትና የገንዘብ መጠን የሚገልጽ በማስረጃ የተደገፈ ሪፖርት በየወሩ ለማኔጅመንቱ ወይም ለሚመለከተው የስራ ሂደት የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

➢ አቅርበናል፡፡

## 8.3. <u>በ2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸውን ግኝቶች በተመለከተ፤</u>

8.4. በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በተደረገበት ወቅት በጥሬ ገንዘብ ጉድለት በገንዘብ ያገኙ በአባያ ካምፓስ ብር 61,238.12 እና በኩልፎ ካምፓስ ብር 47,342.00 በጠቅላላው ብር 108,580.12 በጥሬ ገንዘብ ቆጠራውና በሂሳብ ሪፖርቱ መካከል ልዩነት የሚታይ ሲሆን ገንዘብ ያገኙቹ የታገዱ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ አለመሆኑን፡፡

- ከለጋሽ ድርጅቶች የተገኘው የእርዳታ የገቢ ሂሳብ ብር 2,460,717.53 በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት ያልተመዘገበ፣ የሂሳብ ሪፖርትም ያልተዘጋጀለትና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣ በደብዳቤ ትዕዛዝ እንደተሰጠ የተገለጸ ቢሆንም ማስተካከያ አለመደረጉን፣
- የአርባምንጭ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ ተማሪዎች/TTC program/ በክረምት መርሃ ግብር የስራ ሃላፊዎችና ለተለያየ ክፍል ሰራተኞች ላስተባበሩበትና ለተሳተፉበት በድምሩ ብር 963,243.59 ክፍያው በቦርድ ሳይፈቀድ ከደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈፀሙ፤ ክፍያው የተፈጸመው ከውስጥ ገቢ ሳይሆን ከደ/ብ/ብ/ህ/ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጀት በመሆኑና ዩኒቨርስቲው አገልግሎቱን ለመስጠት ብቻ ውል ገብቶ ከባለበጀት መ/ቤቱ ገንዘብ የተከፈለ መሆኑን ቢገለጽም የውል ማስረጃ አለመቅረቡን እንዲሁም ገንዘቡ ተመላሽ አለመደረጉን ፡፡
- ዩኒቨርሲቲው 16ኛውን የዘላቂ ውሃ ሃብት ልማት ሲምፖዚየም ባዘጋጀበት ወቅት፤በአውደ ጥናቱ ጥናታዊ ጹሑፍ ላቀረቡ፣ የሲምፖዚዬሙን ሂደት የተሳካ ለማድረግ የተለያዩ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉ እንዲሁም ሲምፖዚየሙ ላይ ለተሳተፉ ኮሚቴዎች ሲምፖዚየሙን በመምራት በማስተባበር ለሰሩበት በሚል በድምሩ ብር 109,400.00 ከደንብና ከመመሪያ ውጪ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑን፡፡
- ለአይሲቲ መሰረተ ልማት የሚሆኑ እቃዎች ለኒሮኔት ኃ/የተ/የግል ድርጅት ብር 268,492.88 በብልጫ ክፍያ የተፈፀመለትና ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደግሞ ብር 40,273.94 መግባት ከሚገባው በላይ ገቢ የተደረገ በመሆኑ በጠቅላላው ብር 308,766.82 አላግባብ የሆነ ክፍያ ቢፈፀምም፤ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑን፡፡
- በውሃው ዘርፍ የመምህራን የምርምርና ማስተማር አቅም ለማሳደግ ‹‹Wateroloo Haydrogeologic›› ካናዳ ለሚገኘው የውጭ ድርጅት የአጭር ጊዜ ስልጠና ለ30 መምህራን ለሰጠበት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድሚያ ታክስ /withholding / በድምሩ ብር 230,249.13 ተቀናሽ መሆን ያለበት ታክስ ያልተቀነሰ እና ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ ቢገለጽም አሁንም የእርምት ርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን፡፣

- ዩኒቨርሲቲው በ2008 በጀት አመት ከተለያዩ ድርጅቶች ግዢ የፈጸመ ሲሆን፤ በድምሩ ብር 1,130,945.70 የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያላደረገ መሆኑ፤
- ከራማ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማህበር በዋናው ግቢ ኤሌክትሪካል ወርክሾፕ ግንባታ የጉዳት ካሳ ብር 1,453,714.12 ገቢ ያልተደረገ መሆኑን፡፡

**የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

**ከሰላምታ ጋር**

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

## የ2009 በጀት ዓመት ኦዲት የሥራ አመራር ሪፖርት

**መግቢያ ፣**

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲውን የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት ፣**

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የጥሬ ገንዘብ /ሳጥን ሂሳብ/፣**

1.1. **ሰኔ 30 በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እና በሂሳብ ሪፖርት መካከል ስለሚታየው የሂሳብ ልዩነት፤**

1.1.1. **ግኝት**

*የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/ሀ የሂሣብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ እንዳለበት፤ እንዲሁም በዚሁ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/6 ፊደል መ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጊዜያዊ ሂሳቦች መዝጊያ ምዝገባ ተከናውኖ የዘመኑን ሂሳብ በመዝጋት ቋሚ ሂሳቦች ለቀጣዩ በጀት ዓመት መተላለፍ እንዳለባቸው በሚገልፀው መሰረት ለመሰራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በጀት ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት የሰኔ ወር የባንክ እና ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ወደ ተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) ሙሉ ለሙሉ ያልተመዘገበ እና የባንክ ሂሳብ /የጥሬ ገንዘብ/ የሌጀር ሚዛን ያልታወቀ በመሆኑ፣*

- በኩልፎ ካምፓስ በገንዘብ ያዥች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ የሌለ ሲሆን በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታየው ብር 12,296.35 በመሆኑ በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረው በብር 12,296.35 የሚያንስ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

1.1.2. **ስጋት** ፣

- በጥሬ ገንዘብ ሂሣብ አያያዝና አጠባበቅ ላይ ተገቢው ቁጥጥር ያለማድረግ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

1.1.3. **የማሻሻያ ሃሳብ** ፣

በጥሬ ገንዘብ ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል:: በመሆኑም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተደረገው የጥሬ ገንዘብ ቆጠራና በሌጀርና በሪፖርት ላይ በብልጫ የተመዘገበበት ምክንያት በውስጥ ኦዲት ተጣርቶ ተገቢውን እርምጃ ሊወሰድ ይገባል::

1.1.4. **የስራ አመራሩ ምላሽ**

በኩልፎ ካምፓስ ገንዘብ ያዥና በዓባይ ካምፓስ ገንዘብ ያዥ ላይ በ2008 በጀት ዓመት በጥሬ ገንዘብ ጉድለት በተገኘው ላይ በተጨማሪ አሁንም በ2009 በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት ውስጥ ከላይ የተጠቀሰው የጥሬ-ገንዘብ ጉድለት በኩልፎ ካምፓስ በገንዘብ ያዥ ላይ በመገኘቱ

ዩኒቨርሲቲው በገንዘብ ያገሮች ላይ እርምጃዎችን መውሰድ ጀምሯል፡፡ ስለዚህ በገንዘብ ያገሮችን ገንዘብ ያኘነት ሥራ ላይ ማገድና የድሲፒሊን ቅጣት የተወሰደ መሆኑን እንገልፃን፡፡

2. <u>የገቢ ሂሳብ</u>፣

**2.1. <u>አላግባብ በተከፋይ የተያዘ ከለጋሽ አገሮች በእርዳታ የተገኘው እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ የፕሮጅክት ሂሳብ</u>** ፣

2.1.1. **<u>ግኝት</u>** ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ከውጭ አገር ለጋሽ መንግስታት የሚያገኘውን የብድርና የእርዳታ ገንዘብ ከሚኒስትሩ በቻናል አንድ የገንዘብ ፍሰት የተላለፈውን፣ በመ/ቤቱ ባንክ ቀጥታ ከአበዳሪና እርዳታ ሰጪዎች የገባውን ሂሳብ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ መሰረት የተዘጋጁትን ቻርት ኦፍ አካውንትስ፣ ቫውቸር፣ መዝገቦችና የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጾችን በመጠቀም ሂሳቡን መዝግቦ መያዝና ወርሃዊ፣ የሩብ አመትና አመታዊ ሪፖርት ከባንክ መግለጫው ጋር ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ ያገኘውን የፕሮጀክት ፈንድ

- ከDSS project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 390851 ብር 250,946 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 390852 የተሰበሰበው ብር 238,286፤ በድምሩ ብር 489,232.00፣
- ከSOLAR SAHAY Project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89502 ብር 500,000.00 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89505 ብር 500,000.00 በድምሩ ብር 1,000,000.00
- AEEP Project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 473299 ብር 146,289.00 ፣በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 473300 ብር 72,959.40 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 89501 ብር 9,812.44 በድምሩ ብር 229,060.84፣
- ከNICH project በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487906 ብር 215,242.20 እና በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 488023 ብር 1,336,646.42 በድምሩ ብር 1,551,888.62፣
- ከSouth Design & Supervision በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487907 ብር 399,984.00፣
- ከSTICHTING IHE DELF በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 487941 ብር 258,762.77፣
- ከRift Valley Lakes Basin Authority በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 488013 ብር 20,000.00፣

በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት ገቢው በገቢ አርዕስት ወጪውም በወጪ አርዕስት ተመዝግቦ መያዝ ሲገባው፡ በተከፋይ ሂሳብ በዴቢትና በክሬዲት በማቀናነስ እየተመዘገበ መሆኑ፤

- ከVlir-ous Project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000155953946 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 1,271,513.25፣
- ከVlir-enset project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000134703311 እስከ ሰኔ 30/2008 ድረስ ብር 641,389.69፣
- ከNorhed Project በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000021625918 እስከ ሰኔ 30/2009 ድረስ ብር 433,467.22፣ በድምሩ ብር 2,346,370.16 የእርዳታ የገቢ ሂሳብ ዘመናዊ በሆነና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) የማይመዘገብ እንዲሁም የገቢ፤ የወጪ፣ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴ ምዝገባ፣ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት /Charts of accounts/ መሰረት የማይመዘገብ፣ የሂሳብ ሪፖርት የማይዘጋጅለትና ለሚመለከተው አካል የማይቀርብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

2.1.2. <u>ስጋት፤</u>

- የተሰበሰበዉን ገቢ እንዲሁም ወጪ በተከፋይ የሂሳብ አርዕስት ማሳየቱ የዩኒቨርሲቲው የገቢ እና የወጪው ሂሳብ እንዳይታይ ሊያደርግ ከመቻሉ በላይ የሂሳብ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታውን እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡
- የሂሳብ እንቅስቃሴን ዘመናዊ በሆነ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ካልተያዘ ከፍተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈጅ ከመሆኑ በተጨማሪ ለስህተት የሚዳርግና ስህተቱንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈልጎ ለማግኘትም ሆነ ስህተትን ወዲያውኑ ለማስተካከል እንዲሁም የውስጥና የውጭ ኦዲተሮች የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ ጊዜና ገንዘብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፤

- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች በእርዳታ የሚገኘው የፕሮጀክት ፈንድ በመንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር /Charts of accounts/መሰረት ገቢው በገቢ አርዕሰት ወጪውም በወጪ አርዕስት እየተመዘገበ ተገቢውን የሂሳብ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

- የውስጥ ገቢ የሂሳብ እንቅስቃሴ ዘመናዊ በሆነ የሂሳብ አያያዝ ዘዴና በቴክኖሎጂ ተደግፎ መያዝ ስለሚኖርበት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ዘዴ (IBEX) እንዲያዝ የስራ አመራሩ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.1.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ይህ የሆነው ዩኒቨርሲቲው ከውጪ ሀገር አቻ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን በጋራ ለመስራት በመግባባትና ውል በመፈራረም በተያዘው ጊዜ ገደብ ሪፓርት ለለጋሽ አካላት እያስተላለፉ የሚሰሩበት አግባብ ላይ የተመሠረት ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ከውጪ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ በብሔራዊ ባንክ በኩል ዕውቅና አግኝተውና ምንዛሪው ተመዘግቦ የሚሰራ መሆኑ እንዲታወቅ እያልን የሂሳብ ምዝገባውን በተመለከተ በIBEX ሪፓርት ሥርዓት ያልተዘረጋላቸውና ወደ ዩኒቨርሲቲው በውስጥ ገቢነት እየተሰሩ የሚገኙ የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳብ ሥራዎች ላይ በቀጣይ ከገ/ኢ/ት/ሚኒስተር ጋር በመቀናጀት በኦዲት አስተያየቱ መሠረት በሥራ ላይ የዋለው ገንዘብ በሪፓርት የሚታወቅበት ሁኔታን የምንፈጥር መሆኑን በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ እርምጃ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እናደርጋለን፡፡

## 2.2 <u>ከውስጥ ገቢ መጠቀም በማይቻልባቸው ሁኔታዎች የተገዙ የተማሪዎች የምግብ ግብዓቶች</u>፡-

### 2.2.1 <u>ግኝት</u>

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀጽ 4 ፊደል ሀ እና ለ የውስጥ ገቢን መጠቀም በማይቻልባቸው በመንግስት ውሳኔ የተሰጠባቸው እንደ የተማሪዎችና የህሙማን የምግብ በጀት ተመን ለመሳሰሉት ወጪዎች የውስጥ ገቢን በመጠቀም መግዛት እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው

- በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 2,066,430.27 ለመደበኛና ለክረምት ተማሪዎች አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ የምግብ ግብዓቶች የውስጥ ገቢን በመጠቀም መግዛት በማይቻልበት ሁኔታ ከውስጥ ገቢ ወጪ ሆኖ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ዝርዝር ሁኔታው ከታች በአባሪ ቁጥር 1 ቀርቧል፡፡

### 2.2.2 ስጋት

በመንግስት ታምኖባቸው የሚወጡ መመሪያዎችን መጣስ ተጠያቂነት ያመጣል፡፡

### 2.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲው በመንግስት ታምኖባቸው የወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይኖር ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

### 2.2.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

ይህ የሆነው የክረምት መደበኛ ተማሪዎች የምግብ በጀት በመደበኛ ተማሪዎች ምግብ በጀት 6216 ላይ የማይጨመር በመሆኑና በመደበኛ ተማሪዎች ምግብ በጀት ላይ ከተጨመረ በተማሪዎች ወጪ መጋራት ላይ ተፅእኖ የሚያስከትል ስለሆነ ለዚህ ሲባል ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒሲቴር የክረምት መደበኛ ተማሪዎች የምግብ በጀት በ6412 በውስጥ ላይ የሚሰጠን ስለሆነ በዚህ ምክንያት የተፈፀመ መሆኑን እየገለጽን በቀጣይ በኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት የምናስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

## 2.3 የሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ሂሳብ፤

### 2.3.1 ግኝት

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፡ የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ፣የቤት አበል፣ በአካዳሚክ ዘርፍ በሃላፊነት ላይ ያሉ መምህራን የተለያዩ ጥቅማጥቅሞች እንዲሁም በአስተዳደር ዘርፍ ስር ላሉ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሲፈፀም፤

በዋናው ግቢ የተሰበሰበው ብር 4,404,844.89፤ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተሰበሰበው ብር 5,695,592.05፤ በኩልፎ ካምፓስ የተሰበሰበው ብር 1,099,914.00፤ በነጭ ሳር ካምፓስ የተሰበሰበው ብር 4,027,893.03፤ በአባያ ካምፓስ ከመቀጠር ከሚገኘው ገቢ ግብር ከተሰበሰበው ብር 1,945,906.67፤ በጠቅላላው ብር 17,174,150.64 ከቅጥር የተገኘ ገቢ በሂሳብ መደብ 1101 መመዝገብ ሲኖርበት በሂሳብ መደብ 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች በሚል የተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.3.2 **ስጋት፣**

በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ሪፖርት ካልተደረገ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ ግብሩ ወደ ሚመለከተው ክፍል ባለመግባቱ ገንዘቡን የሚፈልገው ክፍል ያቀደውን ዓላማ ለማሳካት ሊቸገር ይችላል፡፡

2.3.3 **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት የሂሳብ ምዝገባዎች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ለመግባቱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

**2.3.4 የሚመለከተው አካል ምላሽ**

በዩኒቨርሲቲውና በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መካከል የሚደረገው የሪፓርት ሥርዓት የሠራተኞች ሥራ -ግብርና ጡረታ በገቢ ሂሳብ ኮድ 1101 ተመዝግቦ ያለ ገንዘብ ማስተላለፍ የሚመዘገብ ሂሳብ ሥርዓት የሚከተል አሠራር ሲሆን በ5002 ልዩ ልዩ ክፍያዎች ላይ የተሰበሰበው በወቅቱ ለፌዴራል ገቢዎች ተላልፈው በየወሩ ሪፓርት ለገንዘብና ኢኮ/ት/ሚ/ር የሚተላለፍበት አሠራር የምንከተል መሆኑን እየገለፅን በቀጣይ በኦዲት አስተያየቱ መሠረት የምንተገብር መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 3. የወጪ ሂሳብ፣

### 3.1. ደመወዝና ተዛማች ወጪዎች ፣

#### 3.1.1. ከወጪ ሃገር መምህራን ደመወዝ ላይ ያልተቀነሰ ከመቀጠር የሚገኝ ታክስ፣

##### 3.1.1.1. ግኝት፣

በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 ክፍል ሁለት አንቀጽ 13 (መ) በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወይም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በፀደቀ ወይም በተደረገ ስምምነት የተፈቀደ ከመቀጠር የተገኘ ገቢ ከግብር ነፃ ሊደረግ እንደሚችል የተገለጸ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የውጭ ሀገር መምህራን የደመወዝና የጥቅማ ጥቅም ክፍያ ከግብር ነፃ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ሳይኖር ለደመወዝ ሂሳብ ኦዲት በተወሰደ ናሙና መሠረት ለፊሊፒንስ፣ ለጀርመን ፣ለእንግሊዝ እና ለአዉስትራሊያ ዜጎች ከተከፈለዉ ብር 6,100,925.63 ደመወዝ ላይ ብር 1,970,315.76 የሥራ ግብር ተቀናሽ አለመደረጉ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል ፡፣ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ተመልክቷል)

3.1.1.2 **<u>ስጋት</u>** ፣

መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ያሳጣዋል፡፡

3.1.1.3 **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>** ፣

በአዋጁ የውጪ ሃገር መምህራን ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ነጻ መሆናቸውን የሚገልጽ ነገር ባልተገለጸበት ሁኔታ በበጀት ዓመቱ በተከፋላቸው ደመወዝ ላይ ያልተቀነሰው ታክስ ብር 1,970,315.76 ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.1.4 **<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>**

የወጪ መምህራን ቅጥር በአብዛኛው በሕንድ ሀገር በመሆኑና ከሀገራት ጋር ባለው የገቢ ግብር ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ የተደረጉ ቢሆንም ሌሎች በኦዲት ግኝቱ የተጠቀሱ ሀገራት ዘጐች የግብርና ታክስ ስምምነት ጉዳይ ከሚመለከታቸው መረጃ በማስባሰብ ነፃ ሊሆኑ የሚችሉትን ነፃ በማድረግና መክፈል የሚገባቸውን በማስከፈል በኦዲት አስተያየቱ መሠረት በቀጣይ ምላሽ የምናዘጋጅ መሆኑን እንገልፃለ፡፡

3.1.2 **<u>ዘላቂነት ባለው በቋሚ የስራ መደቦች ላይ በቀን ሰራተኝነት የተቀጠሩ ሰራተኞችን በተመለከተ፣</u>**

3.1.2.1**<u>ግኝት</u>** ፣

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ18/22/459 በቀን 16/04/2005 ዓ.ም በኮንትራት /በጊዜያዊ ተቀጥረው የሚገኙ ሰራተኞችን ቋሚ ለማድረግ በወጣው አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በኮንትራት /በጊዜያዊነት ተቀጥረው የነበሩ ሠራተኞች ቅጥር እንዲቋረጥ ሆኖ በአስቸኳይ እንዲሰናበቱና ከየካቲት 30/2005 ዓ.ም በኋላ ቅጥር እንደማይፈፀም እንዲሁም ቅጥር ፈጽሞ የተገኘ የስራ ሃላፊ በህጉ መሰረት ተጠያቂ እንደሚደረግ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ማለትም እንጀራ ጋገሪ፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት መስተንግዶና ጽዳት፣ ወጥ ቤት፣ እህል አበጣሪ፣ አትክልተኛ፣ ሁለገብ ጉልበት ሰራተኛ እና እንጨት ፈላጭ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በቀን ሰራተኝነት በመቅጠር በቀን ብር 22.90 በማሰብ

- በጫሞ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,211,479.65
- በኩፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 214,925.10
- በአባያ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,130,256.23
- በነጭ ሳር ካምፓስ በድምሩ ብር 622,516.50

በጠቅላላው ብር 3,179,177.48 ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

3.1.2.2 <u>ስጋት</u> ፤

- አሰራሩ በመንግስት የበጀት አጠቃቀምና በእቅድ አፈጻጸም ላይ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል፡፡
- ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት የሰው ሃይል በእቅድ እንዳይመራና በመንግስት ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ሊያስከትል ይችላል፡፡

3.1.2.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፤

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒሰቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ ሊመደቡ /ሊቀጠሩ/ይገባል፡፡ በቀን ሰራተኛነት እየተከፈለ ያለው ክፍያም ሊቆም ይገባል፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንተራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ ይኖርበታል፡፤

3.1.2.4 <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ዘላቂነት ባላቸው የስራ መደቦች ላይ የቀን ሰራተኛ ቀጥሮ ማሰራት ተገቢ እንዳልሆነ ዩኒቨርሲቲያችንም ሆነ የስራ ክፍላችን ያምንበታል፡፡ ይሁን እንጂ በ2009 ዓ.ም.በተወሰኑ የስራ ክፍሎች ውስጥ የቀን ሰራተኞች ተቀጥረው እንዲሰሩ ያስገደዱን ነባራዊ ሁኔታዎች ፡-

1. በ2006 ዓ.ም. በተለይም በተማሪዎች አገልግሎት ስር በሚገኙ የስራ ክፍሎች የተፈቀዱ የስራ መደቦች በወቅቱ የነበረውን የተማሪ ቁጥር ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተማሪዎች ቁጥር ከተጠበቀው በላይ በመጨመሩ ባለን የሰው ሃይል ለማስተናገድ አለመቻላችን፡፡
2. በምግብ ቤት አካባቢ የተፈቀዱ አንዳንድ የስራ መደቦች /ምሳሌ ዕጥ መደቦች / ዝቅተኛ ቢሆኑም አገልግሎትና የስራ ልምድ የሚጠይቁ በመሆናቸው ተፈላጊውን የሰው ሃይል በበቂ ሁኔታ ለማግኘት አለመቻላችን፡፡

3. ተጨማሪ የስራ መደቦች እንዲፈቀድልን ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃይል ሚኒሲቴር ጥያቄ ቢቀርብም ከአዲሱ የስራ ደረጃ ምደባ (JEG) ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ አዲስ የስራ መደብ አይፈቀድላችሁም በመባሉ ምክንያት የመማር ማስተማሩ ተግባር እንዳይሰናከል ከማድረግ ጊዜያዊ ሰራተኛ ቀጥረን ለማሰራት የተገደድን መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡
4. በ2010 ዓ.ም. ከዚህ በላይ የጠቃቀስናቸውን ምክንያቶች ለፌዴራል ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃይል ሚኒስቴር በማቅረብ ሁኔታውን በማስረዳት በአንዳንድ የስራ ክፍሎች ላይ የቀን ሰራተኛ እንድንቀጥር ተፈቅዶልን በስራ ላይ መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

### 3.1.3 አላግባብ ለትምህርት ወደ ውጪ ሃገር ለሄዱ መምህራን የተከፈለ ደመወዝ በተመለከተ፣

#### 3.1.3.1 ግኝት ፣

ለትምህርት ወይም ሥልጠና በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር ተልከው ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሠራተኞች ደመወዝ አከፋፈልን በተመለከተ፣ እስከ አንድ ወር ለሚቆይ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር ለሚሄዱ ሙሉ ደመወዛቸው እንዲከፈል ሆኖ ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ጊዜ የሚሄዱት ግን ከተፈላጊ መረጃዎች ጋር ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ ሲፈቀድ በየወሩ ግማሽ ደመወዛቸው እንደሚከፈላቸው ሚያዝያ 20/1990 በቁጥር 80-አጠ52/01/09 ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት መመሪያ መተላለፉ ተገልጾ መስከረም 22/1993 በቁጥር መ19/ጠ49/2/56 ከቀድሞ የፌዴራል ሲቪል ሠርቪስ ኮሚሽን መመሪያው የተላለፈ ቢሆንም፣ በዩኒቨርስቲው የሰው ሃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት በቀረበው መረጃ መሰረት በኩልፎ ካምፓስ ለትምህርት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር የተላኩ ሠራተኛ መምህር ጨንቻ ጨቦ ከእንስሳት ሳይንስ የስራ ክፍል በቀን 20/12/2008 ወደ ውጭ የሄዱ ሲሆን ከመስከረም/2009 እስከ የካቲት/2009 ለ6 ወራት ያለአግባብ ሙሉ ደመወዛቸው ብር (6*10,470.00) 62,820.00 በመከፈሉ በድምሩ ብር **31,410.00** ከመመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል።

#### 3.1.3.2. ስጋት፣

የመንግሥት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅምና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.1.3.2 **የማሻሻያ ሃሳብ ፤**

ከደንብና መመሪያ ውጪ በብልጫ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል። ለወደፊቱም በደመወዝ ክፍያ ወቅት  አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.3.3 **የስራ አመራሩ ምላሽ**

በስህተት የተከፈለው ገንዘብ  ከህግና መመሪያ ውጭ ስለሆነ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ  እናደርጋለን፡፡

3.1.4 **የለቀቁ መምህራንን ክፍያ በተመለከተ፤**

3.1.4.1 **ግኝት ፤**

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ዓ.ም አንቀጽ 12/1 ፊደል ሀ እና ለ መሰረት ለደመወዝ ዝግጅት መሟላት ያለባቸው መረጃ ተሟልተው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡ ከሰው ሃብት አስተዳደር እና ልማት ዳይሬክቶሬት በተሰጠው የለቀቁ መምህራን መግለጫ መሰረት በአባያ እና በኩልፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 33,400.00 መምህራኑ ከዩኒቨርሲቲው ለቀው ሳለ የተከፈላቸው መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የመምህሩ ስም | የስራ ክፍል | ደመወዝ | መምህሩ የለቀቁበት ቀን/ወር/ዓ.ም | መምህሩ ለቀው የተከፈላቸው | አለአግባብ የተከፈለው የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቱሉ ታደሰ | እፅዋት ሳይንስ | 6,570.00 | መስከረም30/2009 | የጥቅምት | 6,570.00 |
| 2 | ፀጋዬነሽ ጳውሎስ | የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ | 10,470.00 | መስከረም30/2009 | መስከረምና ጥቅምት | 10,470.00 |
| 3 | ዶ/ር አበበ ግርማ | ባዮሎጂ | 16,360.00 | ግንቦት30/2009 | የሰኔ | 16,360.00 |
| | | | | | ድምር | 33,400.00 |

3.1.4.2 ስጋት ፣

የመንግሥት ገንዘብ ለግለሰብ ጥቅምና ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.1.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ከደንብና መመሪያ ውጪ በብልጫ የተከፈለው የመንግስት ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል። ለወደፊቱም በደመወዝ ክፍያ ወቅት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

3.1.4.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

የስራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡንተቀብሎታል ፡፡

3.2 ለእቃና አገልግሎት ግዥ፣

3.2.1. የዋጋ ማቅረቢያ ግዥን በተመለከተ፣

3.2.1.1. ግኝት፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/1፣ እና አንቀጽ 24.3 ፊደል ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 24.12 እንደ ቅደም ተከተላቸው፡ የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፡፡ ሆኖም ሊታቀዱ ያልቻሉ እና ዋጋቸው ታህሳስ 12/2008 ዓ.ም ተግባራዊ እንዲደረግ በተደረገው የተሻሻለው መመሪያ ለእቃብር 200,000.00 ለአገልግሎት ግዥ ብር 150,000.00 በእነዚህ ገደብ ውስጥ የሚገመቱ ግዢዎች በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ መፈጸም እንደሚቻል፣ የመንግስት መ/ቤቱ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ተሳታፊዎች በዙሩ የመወዳደር እድል ማግኘታቸውን እና ለመ/ቤቱ ጠቃሚ የሆነ የተለየ ሁኔታ መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አንድ ወይም የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ እንደሌለባቸው፣ እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቱ የዋጋ ማቅረቢያ በመስጠት እና ዋጋ በመወሰን ሂደት ሊፈጠር የሚችል መመሳጠርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር በመከተል እና መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር፣ በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገቢያ ጥናትን በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ማመን እና በየጊዜው ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ከፋፍለው መግዛት እንደሌለባቸው ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተገዙትን እቃዎች/አገልግሎቶች / ኦዲት ሲደረግ ፡

- በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 17,667,845.32፣ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በድምሩ ብር 8,632,655.12፣ በጫሞ ካምፓስ በድምሩ ብር 7,368,645.17፣ በነጭ ሳር ካምፓስ በድምሩ ብር 1,645,104.50፣ በአባያ ካምፓስ በድምሩ ብር 4,344,919.73 እና በኩልፎ ካምፓስ በድምሩ ብር 1,244,558.58 በጠቅላላው ብር **40,903,728.42** አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም ሲገባ ተከፋፍለው በዋጋ ማቅረቢያ ብቻ የተገዙ መሆኑን
- በሁሉም ግቢዎች በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች ትክክለኛ የሆነ የገበያ ጥናት በማድረግ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ግዥው እየተፈጸመ አለመሆኑ፣ በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 3 ቀርቧል፡፡

### 3.2.1.2. <u>ስጋት፣</u>

- ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡
- በግዥ ስራ ክፍሉ የተደረገው የገቢያ ጥናት ዋጋ እና በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ትክክለኛው የገቢያ ዋጋ ሳይታወቅ የሚፈጸም ግዥ ዋጋው የተጋነነ እና መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡

### 3.2.1.3.<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

- ዩኒቨርሲቲው ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም አለበት፡፡
- ዩኒቨርሲቲው በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም አለበት፡፡

### 3.2.1.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

- በዩኒቨርሲቲው የሚያስተዳድራቸው 6 ካምፓሶች ከሚያስተናግዳቸው 20 ሽህ መደበኛ ተማሪዎች ምክንያት በየጊዜው ያልታቀዱና ያልታሰቡ ደራሽ ስራዎች ሲያጋጥሙት(የመብራት የውሃ ድንገት መቋረጥ የፍሽ መስመሮች ድንገት መፈንዳት) ምክንያት የጥገና እቃዎች በእቃ ግምጃ ቤት ሳይገኝ ከቀረ በዩኒቨርሲቲው የዋጋ ጥናት ባለሙያዎች የገበያ ዋጋ እያሰጠና ግዥ የሚፈጽም ሲሆን በመመሪያው እንደተጠቀሰው የኤጀንሲው ድረ -ገጽ የሚወጡ ዋጋዎች ትላልቅ የሆኑ የካምፓኒ ምርቶች እንጂ የትናንሽ እቃዎች የማይገኙ ከመሆናቸውም ባሻገር ወቅታዊ አለመሆናቸው ለአጠቃቀም ችግር መሆኑ ሲሆን ሌሎች ትናንሽ ህትመቶች ለግልጽ ጨረታ በማያመች ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ለክፍሎ ግዥ እንዲፈፀም በመላካቸውና ለየብቻ ሲታዩ ለግልጽ ጨረታ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑና በግልጽ ጨረታ ቢወጣም ጊዜ ከመውሰዱ በስተቀር ተወዳዳሪዎች የማይስብ በመሆኑ በዋጋ ማቅረቢያ ለመግዛት የሚያስቸግረን በመሆኑ የተፈፀመ ሲሆን በቀጣይ በኦዲት ማሻሻያው መሰረት በአመቱ መጀመሪያ ታቅደው እንዲቀርቡና በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ጥረት እናደርጋለን፡፡ በተጨማሪ በዩኒቨርስቲው የግዥ ጥያቄ የሚቀርበው በቅድሚያ ታቅዶ ሳይሆን በሰነዱ ላይ የተገለጸው ቀን የግዥ ጥያቄው የቀረበበትን ቀን በግልጽ እንደሚያሳየው በተለያየ ቀናትና ወራት የቀረቡ እንጂ በአንድ ግዜ ጥያቄ ያልቀረቡ በመሆኑ እንደ አመጣጣቸው በፐርፎርማ እንዲገዙ ግዥ ክፍሉ ላይ ጫና በማድረግ የተፈፀመ ግዥ ነው፡፡ ይህ ግዥ በግዢ ክፍሉ ላይ ከፍተኛ የስራ ጫና ከመፍጠሩም በላይ የዋጋ መጋነን ችግርን በተደጋጋሚ እያጋጠመን በድጋሚ ለመሰብሰብ የሚገደድበት ወቅትም ያለ ቢሆንም ጥያቄው ሲቀርብ ግዥ ክፍሉ በፐርፎርማ ባይገዛ የመማር ማስተማር ስራውን እያደናቀፈ ነው በሚል በበላይ ኃላፊዎች ጭምር የሚገደድ በመሆኑ የተፈጠረ ችግር ነው ፡፡ እንዲሁም በአካባቢ ጨረታ/በፐሮፎርማ የግንባታ ስራዎች የተለያዩና በአንድ ጊዜ ተጠይቀው የሚቀርቡ ባለመሆናቸው አጠቃልሎ በግልጽ ጨረታ መግዛት አልተቻለም፡፡ የግንባታ ጥያቄው የሚቀርበው በአመቱ መጀመሪያ ያስፈልጋል ተብሎ የተያዘ ሳይሆን በየጊዜው ችግር ሲገጥም እየታየ እንዲሰራ ለክፍላችን ሲደርስ የዋጋ ማቅረቢያ የግንባታ ጣሪያን ሳይዘል ማህበራትን በማወዳደር የተፈፀሙ ስራዎች ናቸው፡፡ የሚቀርቡት አንዳንድ ስራዎች አስቸኳይ በመሆናቸው ሌሎች ጥያቄዎች እስከሚቀርቡ ለማሰባሰብ ቢሞከር የተፈጠረው ችግር ጊዜ የማይሰጥ መሆኑ ነው፡፡ ለመጥቀስም ያህል፡-

- ለለተማሪው ማጥኛ ቦታዎችን ውብና ሳቢ ለማድረግ በሚል በሁሉም ካምፓሶች በራሳቸው አወዳድረው  ውልና አዋርድ በማእከል እንዲሰጥ በማለት ሳይታቀድ በድንገት የተሰጠ የስራ መመሪያ መሆኑ፡፡
- የቆሻሻ ማስወገጃ ሴፍቲክ  ታንክ ፍሳሹ በድንገት  በመፈንዳት ሲያስቸግር ግንባታው በአስቸኳይ  እንዲገነባ በመደረጉ በግልጽ ጨረታ ለመፈፀም ረዥም ጊዜየሚወስድ በመሆኑና ችግሩ ደግሞ ጊዜ የማይሰጥ መሆኑ ነው፡፡
- በአጠቃላይ  በግልጽ ጨረታ ለመግዛት በአመቱ መጀመሪያ  ታቅዶና አስቀድሞ ዝርዝሩ ቀርቦና አጠናቅሮ መግዛት ሲቻል በአመቱ በተለያየ ጊዜ አነስተኛ የግንባታ ስራዎች  በመሆናቸውና በአስቸኳይ እንዲጠገኑ/እንዲሰሩ በመጠየቁ የተፈፀሙ ግዥዎች መሆናቸውን  እንገልፃለን፡፡

<u>በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ማኔጂንግ ዳይሬክተር የተሰጠ ምላሽ</u>

- አስቀድሞ ማቀድ ከተቻለ የመንግሥት መ/ቤቶች ለአገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎችን በግልፅ ጨረታ ግዥ ዘዴ መፈፀም አለባቸው ተብሎ የተሠጠው አስተያየት ትክክልና የምንቀበለው ነው፡፡ በኢንስቲትዩቱም ይህንን የግዥ አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የዓመቱን አጠቃላይ የግዥ ዕቅድ ለዩኒቨርሲቲው ግዥና ንብረት አስ/ር ዳይሬክቶሬት የላክን ቢሆንም በማዕከል የጨረታ መጓተት ምክንያት የተጠየቁ አብዛኛዎቹ የጥገና ዕቃዎች፣ የግንባታ ዕቃዎች፣ የተማሪዎች ካፍቴሪያ አገ/ት ዕቃዎች በወቅቱ ሊቀርቡልን አልቻሉም ስለሆነም ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ለማረጋገጥና የተቋሙን ህልውና ለማስቀጠል ሲባል፡-
- የተማሪዎች ማደሪያ ህንፃዎች፣ መማሪያ ህንፃዎችና ካፍቴሪያ ህንፃዎች ውስጥ የሚገኙ የውሃ፣ መብራትና ፍሳሽ መሥመሮች ያረጁ በመሆናቸው በክረምት የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ወቅት የጥገናና ዕድሳት ሥራዎች ካልተሰሩ በቀጣዩ ዓመት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር አዳጋች ስለሚሆን ለዚሁ የጥገናና ዕድሳት አገልግሎት የሚውሉ ነገር ግን በማዕከል ጨረታ ሊቀርቡልን ያልቻሉትን በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንትና በኢንስቲትዩቱ አስ/ር ካውንሲል በተሰጠው ይሁንታ መሠረት ግዥው የተፈፀመ መሆኑ፡
- በዋናው ግቢ ከግንባታ ሥራዎች ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን መጥፎ የሆነ ምድረ-ግቢ ገፅታ በመቀየር ምቹና ሳቢ የሆነ የሥራ አከባቢ ለመፍጠር ታስቦ በተደጋጋሚ

በአከባቢ ጨረታ ለማሠራት ጥረት ቢደረግም እጅግ በጣም የተጋነነ ዋጋ በማቅረባቸው ምክንያት ሥራውን ማሠራት አልተቻለም፡፡ በመጨረሻም የኢንስቲትዩቱ አመራሮች የትም/ት ክፍል ባለሙያዎችን በማነሳሳት በነፃ የዲዛይን ሥራ እንድሠሩ በማድረግ እንድሁም ተከታትሎ የማሠራቱንም ሥራ እንድሠሩና ተቋሙም ለሥራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብዓቶችንና ማሽኖችን እንድያቀርብ ለዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ባቀረብነው ኘሮፖዛል መሠረት የዩኒቨርሲቲውም ማኔጅመንት ይሁንታ በሠጠው መሠረት የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች፣ የጥገና ዕቃዎችና ማሽኖች የተገዙ መሆኑን

- ከመማር ማስተማር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው እንደማባዣ ማሽኖች ያሉትን በተመለከተ በወቅቱ አገልግሎት ይሠጡ የነበሩ አሮጌ የማባዣ ማሽኖች ድንገት በፈተና ወቅት በመበላሸታቸው ምክንያት የፈተና ሂደቱ እንዳይስተጓጐል ችግሩን ለዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት በማስረዳት ግዥው በኢንስቲትዩቱ በኩል ተፈፃሚ እንድሆን ማኔጅመንቱ በሠጠው ይሁንታ መሠረት የተፈፀመ መሆኑን፡
- ለሲምፖዚየም አገልግሎት ታስበው የተገዙ የህትመትና የቦርሳ ግዥዎችን በተመለከተ በመጠንና በዓይነት ደረጃ ሲታይ ትንሽ ስለሆኑ በግልፅ ጨረታ ሂደት ውስጥ ሊፈጠር የሚችለውን መጓተት ስጋት ውስጥ በማስገባት የተፈፀመ መሆኑን፡
- ለተማሪዎች ምግብ ቤትና ለአርክቴክቸር ትም/ት ክፍል የተገዙ የሸራና የትም/ት ግብዓቶችን በተመለከተ ዕቃዎቹ በሥራው ባህሪ ለዋናው ግቢ ምግብ ቤትና ለአርክቴክቸር ትም/ት ክፍል ብቻ የሚያስፈልጉ በመሆናቸው በዓይነትና በመጠን ትንሽ ናቸው፡፡ ስለሆነም እንደ ዩኒቨርሲቲ በግልፅ ጨረታ ለመግዛት ከዚህ በፊት ተሞክሮ ውጤታማ ሊሆን ባለመቻሉ የትም/ት ሥራው እንዳይስተጓጐል ሲባል የተፈፀመ ግዥ መሆኑ፣
- በጥቅሉ ሲታይ የኢንስቲትዩቱን የዓመቱን ግዥ ዕቅድ አዘጋጅተን በወቅቱ ለዩኒቨርሲቲው ግዥና ንብረት አስተዳደር በላክነው መሠረት ውስን ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ ሲገዙ አብዛኛዎቹ በኦዲት ሪፖርት ላይ የተዘረዘሩ ዕቃዎች ወቅቱን ጠብቀው ሊቀርቡልን ባለመቻሉ የተቋሙን ህልውና ለማስቀጠል ሲባል በዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንትና በኢንስቲትዩቱ አስተዳደር ካውንስል ይሁንታ አግኝቶ የተፈፀሙ ግዥዎች መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

## በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ዲን የተሰጠ ምላሽ

- በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴን መፈፀም ያልቻልንበት ምክንያት

1. የማዕቀፍና የማዕከል ግዥዎች ለመማር ማስተማረ ሥራ ወቅቱን ጠብቆ ስለማይደርስ ነው
   - ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከጀመሩ በኃላ ለትምህርት የሚያገለግሉ ግብአቶችን በግዜ ስለማይደርሱልን ሳንወድ በግድ ወደ ፕሪሮርማ ግዢዎች ውስጥ የገባነው፡፡
   - የመማር ማስተማሩ ስራ እንይስተጓጓል ሌላ አማራጭ ስለሌለን ተገደን ነው
2. በኮሌጁ ውስጥ በግዥ ክፍል የገበያ ዋጋ የሚጠና ባለሙያ ባለመኖሩ ምክንያት ኮሌጁ በኮሚቴ ነው የገበያ የምስጠናው እና የገበያ ዋጋ ላይ ጥብቅ ክትትል እያደርግ እንገኛለን
3. የኤጀንሲውን ድረ-ገፍ በተመለከተ ብዙ ግዚ ለማየት እየተሞከረ ቢሆን በብዛት እቃዎችን ማግኘት አልተቻለም ለወደፊቱ ትኩረት ሰተንበት እንጠቀማለን የተወሰኑ አራብዎችን ብቻ በተደጋጋሚ የሚጋበዙ ሣይሆን በጫሞ ካምስ ውስጥ ያለው 2 ኮሌጅና 2 ት/ቤት በአንድ ላይ ስለሆነ የአስተዳደር ሠራተኞች የካምፓሱን ስራዎችን በጋራ ስለሚሰሩ ለኮሌጆች ሆለ ለት/ቤቶች ተመሳሳየ ዕቃዎች ሲገኑ በአንድ በፕሮማ ለነጋዴች ስለሚሰጥ እና ስለሚወዳደሩ እንጂ በተደጋጋሚ ተጋብዘው አለመሆኑን እገልፃለው ለወደፊቱ እርምት እንወስዳለን፡፡

## በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን የተሰጠ ምላሽ

በአባሪ 1 ላይ ከ ቁጥር 1-8 የተጠቀሱት ኮሌጁ ለማዕቀፍ ግዥ በየአመቱ እቅድ አውጥቶ ቢያቀርብም በወቅቱ ግዥዎች ባለ መፈፀማቸዉ ብዙ ስራ እየተጓተተ በመቸገራችን ምክንያት የግዥ ህግና ደንብ ተጠብቆ ግዥዎች ተካሂደዋል፡፡ ወደፊት የማዕቀፉ ግዥ መጓትተ ከቀረ ወደ ማዕቀፍ ግዢ ላይ በመተማመን በወቅቱ ዕቃዎች እንዲደርሱልን ከተደረገ የተሻለ ይሆናል፡፡ ከቁጥር 9-12 የተጠቀሱት አቅራቢዎች የህክምና እቃ አቅራቢዎች በመሆናቸው የሚቀርበው የህክምና ዕቃ የሚገዛው ለህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብቻ በመሆኑ የማዕቀፍ ግዥ ሳይሆን በኮሌጁ ነው ግዥ የተፈፀመው፡፡ የህክምና ዕቃዎችን በአብዛኛዉ የምንገዛዉ ከመንግስት አቅራቢ ከሆነው የኢትዮጵያ የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ሲሆን እንርሱ ማቅረብ

ያልቻሉበትን ወይም እነርሱ ደርጅት የሌሉ የህክምና ዕቃዎችን ብቻከእነርሱ ድርጅት ዕቃዎቹ አለመኖራቸዉን ማረጋገጫ ሲሰጡን ብቻ ነዉ፡፡ ከሌሎች አቀቅራቢዎች ከአሁን በፊትም የተገዙት ቢሆን የግዥ ህግና ደንብን የተከተለ ግዥ ነዉ የተፈፀመዉ፡፡ በአጠቃላይ  በኦዲት መወሰድ አለባቸዉ የተባሉት አስተያየቶች ተገቢ በመሆናቸዉ ወደፊትም በምናካሂዳቸዉ ግዥዎች ተፈፀሚ እንደሚደረጉ እናሳዉቃለን፡፡

<u>የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ዲን የተሰጠ ምላሽ</u>

- ተሽከርካሪን በተመለከታ፡- ለትምህርት ጉዞ መስክ የሚሄዱ ተማሪዎች ትም/ክፍልሉ በሚጠይቀው መሠረት ተሽከርካሪ እንዲቀርብ ለዩኒቨርሲቲ ጠቅላላ አገልግሎት ዳ/ጽ/ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ማቅረብ እንደማይችሉ ሲያረጋግጡ ብቻ ወደ አገልግሎት ኪራይ መግባት አስገዳጅ ይሆናል፡፡ በዚህ ግዜ ያሉ መስመሮችና ምልልሶች በግልጽ በማስቀመጥ ፕሮፎርማ ተሠብስቦ ለተጠየቀው ጥራት ያለው አገልግሎት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ አሸናፊ ይሆናል፡፡ በተቻለ መጠን የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ለዚሁ አገልግሎት ቢሠማሩ ችግሩ በዘለቄታው ሊፈታ ይችላል፡፡
- የቤተ-ሙከራ ኬሚካሎችና ቁሶችን በጥቅል በግልጽ ጨረታ መግዛቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከቤተ-ሙከራዎች መብዛት /30/ እና ከሚጠቀሙት ኬሚካል ተለያይነት በብዛትም በአይነትም የተነሳ በግራም ከሚገዙ እስከ አላቂ የሆኑ የቤተ -ሙከራ መሳሪያ ጋዞች ድረስ ውስብስብ በመሆኑ የመማር ማስተማሩ በተግባር የተደገፈ እንዲሆን በ8 ትምህርት ክፍሎች የሚገኙ 40 ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ በመሆኑ ለአፈፃፀም በመቸገራችን መሆኑ ቢታወቁልን ከቅድመ ምረቃ ባሻገር  የድረ ምረቃ ምርምር ስራዎች የኬማካልና ቁሳቁስ ፍላጎት እንደ ምርምር አይነቱ ሠፊ ተለያይነት ያለው በመሆኑ ይህ በየፕሮግራሙ ሲከፋፈል  ጥቂት መሆኑ ቢታወቅ
- የንጽህና መስጫ እቃዎች በጥቅል ግዥ በማዕከል እንዲገዙ ሲደረግ በወቅቱ ካለመቅረባቸው የተነሣ በእለት ተእለት አስፈላጊ በሆኑ ግብአቶች ሳሙና፣ኦሞ፣ Vim----- የመሳሰሉት በተማሪዎች መግብ ቤት አካባቢ መጓደላቸው የሚፈጥረውን አደጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ማስታገሻ ግዥዎችን ለመፈፀም እንገዳዳለን፡፡ በመሆኑም የማዕከል ግዥ ማዘግየት በነባራዊ ሁኔታው መሬት ላይ ፊት ለፊት

እየገጠመን ያለው ችግር ምክንያት ስለማይሆን የማስታገሻ እርምጃ መውሠድ ተገደናል፡፡

<u>የግብርና ሳይንስ ኮሌጅ ዲን የተሰጠ ምላሽ</u>

የአላቂ ዕቃ ግዥዎችን ሂደት በተመለከተ በጥቅል ግዥ የተጠየቁ የተለያዩ ዕቃዎች በወቅቱ መቅረብ ባለመቻላቸው ምክንያት እየተከናወነ ያለውን ሰላማዊ የመማር ማስተማር ስራ እንዳይስተጓጎል ወይም ሂደቱ እንዳይዛባ የሚያስልጉ ዕቃዎች በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴን በመጠቀም ግዥው ሊከናወን ችሏል፡፡ ሌሎች ከጥገና ጋር ተያይዞ የተፈጸሙ ግዥዎችን በተመለከተ ካምፓሶችን የመማር ማስተማር ስራዎችን እያከነወነ ያለው ገና የግንባታ ሂደት በካምፓሰ ውስጥ ባላለቀበት ሁኔታ ይህም ሲባል ቀድሞ በካምፓስ ውሰጥ የነበሩት የአግልግሎት መሰረተ ልማቶች ለረዥም ጊዜ ያገለገሉ በመሆኑ ጥገና ስራ ሥለሚያስልጋቸው ከዚህም በተጨማሪ ካምፓስ ውስጥ የሚከናወነው አዲስ የግንባታ ስራ በነዚህ መሰረተ ልማቶች ላይ ተደጋጋሚ የመቆራረጥና የመበላሸት ምክንያት ሆኗል፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክንያት እነዚ አገልግሎቶች እንዳይቋረጡ ከዚያም አልፎ ብሶትና ሁከት በተማሪዎች ዘንድ እንዳይፈጠር ሲባል የዋጋ ማቅረቢያ ግዢ ዘዴን በመጠቀም ግዢዎችን ልንፈፅም ችለናል በቀጣይ ግን ከገጠመን ችግር በመነሳት ከወዲሁ አስቀድመን በማቀድ የግልጽ ጨረታ ግዥ ዘዴን እንደምንጠቀምና የተሰጠውን የማሻሻያ ርምጅ ተግባራዊ የምናደርግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

### 3.2.2. <u>ያለውድድር በቀጥታ የተገዛ  የዕቃና የአገልግሎት ግዥን በተመለከተ</u> ፣

#### 3.2.2.1. <u>ግኝት፣</u>

ሰኔ/2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥአፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15.2-15.4 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ የመንግስት መ/ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ እንዲሁም ከግልጽ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች የሚጠቀም ማናቸውም የመንግሥት መ/ቤት በእነዚህ ዘዴዎች ለመጠቀም የመረጠበትን ምክንያትና ሁኔታዎች የሚገልጽ ሠነድ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል። ይሁን እንጂ ግዢዎች በመመሪያው መሰረት መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ  ዩኒቨርሲቲው፣ በዋና

ግቢ በድምሩ ብር 1,006,884.30 ዕቃ እና አገልግሎት ግዥ በውስን የጨረታ መፈፀሙን፤ (የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 4 ቀርቧል፡፡)

3.2.2.2. ስጋት ፤

- ግዥ በመመሪውያ መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም፣ ይህምቁጠባን፣ የአፈፃፀም ብቃትንና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብም ለምዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

3.2.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ዩኒቨርሲቲው ማናቸውንም የአገልግሎት ክፍያ ሲፈጽም በመንግስት የግዥ አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት ሊፈጽም ይገባል፡፡ በመሆኑም ወደ ዩኒቨርሲቲው የሚመጡ እንግዶችን ባላቸው የኃላፊነት ደረጃ ለማስተናገድ ሲባል የወጣው ወጪም በውድድር፣ ካልተቻለም በልዩ ሁኔታ የሚመለከተውን አካል በማስፈቀድ መፈጸም አለበት፡፡

3.2.2.4. የሚመለከተው አካል ምላሽ

በግዥ አገልግሎትና የንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር የተሰጠ ምላሽ

- ለህዳሴ ዋንጫ አቀባበል ከጋሞገፋ ዞን አስተዳደር ጋር በመሆነ በጋሞ ጎፋ ዞን ውስጥ የሚገኙ 5 ብሄር ብሄረሰቦች ባህላዊ አልባሳት የዝግጅት ቀኑ 3 ቀናት ብቻ ሲቀረው ተሰርቶ እንዲቀርር የተደረገ ጥያቄ በመሆኑ በማወዳደር ቢሞከር ሊደርስ ባለመቻሉ እና በቂና የተዘጋጀ አልባሳት ካሉት የባህል ልብስ አዘጋጅ ድርጅት በ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ፍቃድ የተፈፀመ ግዥ ነው፡፡
- የታሸገ ውሃ የተገዛው ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለሰራተኞች በመስከረም ወር በአገር አቀፍ ደረጃ በሚሰጠው ስልጠና ውሃ እንዲያቀርብ በአስቸኳይ በመጠየቃችን ስልጠናው ከተጀመረ በኋላ የቀረበ ጥያቄ በመሆኑ በጨረታ መግዛት ባለመቻሉ ፕሬዝዳንቱን በማስፍቀድ የተፍጸመ ነው፡፡

3.2.3. የለቀማ የግዥ ዘዴን መስፈርት ያላሟላ ግዥ፣

3.2.3.1. ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 6 በአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሰ) መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈፀም ግዥ ለጥናትና ለምርምር አገልግሎት የሚፈለግ እና ከመደበኛ አቅራቢዎች የማይገኝ ወይም በለቀማ ቢገዛ ለመ/ቤቱ የኢኮኖሚ ጥቅም እንደሚያስገኝ ሲረጋገጥ ከፊደል "ሀ እስከ ሰ"

የተዘረዘሩትን አሰራሮች በመከተል የለቀማ ግዥ መፈፀም እንደሚቻል በተገለፀው መሰረት ከገበያ በለቀማ የሚፈጸመው ግዥ በመመሪያው የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች በመከተል የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በዋናው ግቢ በተለያዩ የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች እና የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 1,373,129.12፣ (ዝርዝር ሁኔታው በአባሪ ቁጥር 5 ቀርቧል፡፡)

- በጫሞ ካምፓስ
  - የተገዙት ከረሻት፣ የታሸገ ውሃ እና መፅሀፍት ከአንድ አቅራቢ ብቻ እንደሚገኙ የሚገልፅ ወይም በሌላኛው ድርጅት ላለመገኘታቸው ማስረጃ ሳይቀርብ ያለውድድር ግዥው በለቀማ ብቻ የተፈፀመ መሆኑ፣
  - ግዥዉን በለቀማ ሊገዙ የሚችሉ ብዛታቸው ከሶስት ያላነሱ ጊዜያዊ የኮሚቴ አባላት በደብዳቤ ቢሰየሙም በገበያው ውስጥ ካለው አቅርቦት የተሻለ ጥራት እና ዋጋ ያላቸውን አቅራቢዎች በመምረጥ እና ዋጋ በማወዳደር ግዥው መፈጸም ያልተቻለበትን ምክንያት የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

3.2.3.2. <u>ስጋት</u> ፣

መንግስት ያወጣቸውን አዋጆች፤ ደንቦችና መመሪያዎችን መተላለፍ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

3.2.3.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ማንኛውም ግዥ በመመሪያው መሠረት እንዲፈፀም የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡

3.2.3.4. <u>የሚመለከተው አካል ምላሽ</u>

<u>በግዥ አገልግሎትና የንብረት አስተዳደር ዳይሬክተር የተሰጠ ምላሽ</u>

- የውሃ ግዥ በአስቸኳይ እንዲፈጸም የተደረገው በ2009 መስከረም ላይ ለመምህራን ሰራተኞችና ተማሪዎች ስልጠና እየተካሄደና ከተጀመረ በኋላ ውሃ እንዲቀርብ በመታዘዙ በጨረታ መግዛት ባለመቻሉ ግዜ ባለመኖሩ የተደረገ ነው ፡፡
- የከረሻት ግዥ የተፈጸመው የትምህርት ሚኒስቴር በጠራው ከፍተኛ አመራር ላይ መምህራን መስከረም ት/ት ሲጀመር ጋውን እንዲሁም የዩኒቨርስቲው አርማና ስም

ያለበት ከረቫት ተገዝቶ ለብሰው እንዲገቡ ባስቸኳይ እንዲዘጋጅ በመጠየቁና ይህንንም በጨረታ ለማስኬድ ባለመቻሉ የተፈጸመ ግዥ ነው፡፡

3.2.4. <u>በውሉ መሰረት እቃው ገቢ ባለመሆኑ</u>

<u>ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልሆነ የጉዳት ካሳ</u> ፣

3.2.4.1. <u>ግኝት</u>፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት አቅራቢው በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕቃውን፣ የምክር አገልግሎቱን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን ወይም አገልግሎቱን አጠናቅቆ ባያስረክብ፣ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በአቅራቢውና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት አቅራቢዎች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፡

ዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት አመት ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር ውል በመዋዋል የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ የፈጸመ ሲሆን፤ አቅራቢዎች በውሉ መሠረት ዕቃዎችን ለዩኒቨርሲቲው ማስገባት ከነበረባቸው ቀናት ላሳለፉአቸው ቀናት በየቀኑ የውሉ 1/1000 ቅጣት፣ ከመህቡብ ጀነራል ትሬዲንግ ብር 7,260.00፣ ከዶልቼ ኢንጂነሪንግ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 778,767.42፣ ከአይኢ ኔትዎርክ ሶሉሽንስ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 910,516.17፣ ከጣሰው አንዳርጌ አጠቃላይ የጽህፈት መሳሪያ መሸጫ ብር 3,120.01፣ ከሰላም ሃዋሳ ቢዝነስ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 13,745.94፣ ከአብይ ብርሃኑ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻ ብር 69,300.00፣ ከፍይን ኬሚካል ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 114,002.57፣ ከቴክ ፋይፍ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 3,058.88፣ ከኤምሂር ኢንጂነሪንግ ኢንተርፕራይዝ ብር 1,373,917.04፣ ከባዮቬት ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 76,185.07፣ ከእያሱ ጉልማ ብር 2,186.89፣ ከፓልስ ጠቅላላ ንግድ ድርጅት ብር 52,791.66፣ ከሪሊያብል የት/ት መሳሪያ አቅራቢ ብር 14,629.61፣ ከሶላሪስ ፓወርና አይሲቲ ኃ/የተ/የግ/ማ ብር 25,749.06 ከየትም ሱፐርማርኬት ብር 22,231.55 እና ከሀፌስ ሀሰን የህንጻ መሳሪያ

ብር 12,629.40 በድምሩ ብር 3,480,091.25 የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡ (የሂሳቡን ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቁጥር 6 ቀርቧል)

3.2.4.2. ስጋት፣

አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት በጨረታ ያሸነፉትን ንብረት ገቢ እንዲያደርጉ ካልተደረገ ዩኒቨርሲቲው ከገዛው ዕቃ ሊያገኝ ያቀደውን አገልግሎት እንዲያጣ ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በሥራ አፈጻጸሙ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥርበታል፡፡

3.2.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ ፣

ዩኒቨርሲቲው ከላይ የተመለከተውን ብር 3,480,091.25 አቅራቢዎቹ (ድርጅቶቹ) እንዲከፍሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ካላቀረቡ በመመሪያው መሠረት መክፈል ያለባቸውን የጉዳት ካሳ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

3.2.4.4. የሚመለከተው አካል ምላሽ

ይህን በተመለከተ የግዥ ውል የሚያስተዳድረው የግዥ አገልግሎትና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመሆኑ እያንዳንዱን ዕቃ አቀርቦት ከውል ጊዜው ጋር አመሣክሮ ለመመሪያ በተቀመጠው መሠረት መፈፀም ሲገባ የቀረና በፋይናንስ በኩልም ክፍያ ሙሉ በሙሉ ከመለቀቁ በፊት የካሳ ክፍያ ተቀናሽ መሆኑ እንዳለበት መገለፅ ሲገባ የቀረ ስለሆነ በቀጣይ በዚህ ኦዲት ግኝት መሠረት የምንፈፅም መሆኑን እንገልፃለን፡

3.2.5. በማዕቀፍ ስምምነት የተፈጸመ የተማሪዎች ምግብ ግዥን የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ፤

3.2.5.1. ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 16 ን.አ.16.14.2 ፊደል ለ) በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ የሚያስችል መነሻ እና የተለወጠ ወቅታዊ ዋጋ ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚሰጥ ሲሆን እንዲሁም 16.14.4 በመንግስት መ/ቤቶች በማዕቀፍ ስምምነት ለሚፈጸም ግዥ ዋጋ ማስተካከያ ሊያደርጉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ሀ) የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግባቸው ኤጀንሲው ወይም ማዕከላዊ ስታትስክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የዋጋ መረጃ ለሚሰጥባቸው አቅርቦቶች ብቻ መሆን እንዳለበት ለ)

በማዕቀፍ ስምምነት መሰረት ተፈጻሚ ለሚሆን ግዥ የሚቀርብ የዋጋ ማስተካከያ ጥያቄ መቅረብ የሚኖርበት ስምምነቱ ስራ ላይ ከዋለ ከ3 ወራት በኋላ ሊሆን እንደሚገባ ሐ) የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበትን ዕቃ ወይም አገልግሎት አስመልክቶ ጨረታው በተከፈተበት ዕለት የነበረው ኤጀንሲው ወይም የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የሚያወጣው ዋጋ እና የማዕቀፍ ስምምነቱ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረግበት ጊዜ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ መገለፅ እንደሚኖርበት መ) የመንግስት መ/ቤቱ በውሉ ላይ በተገለፀው እና በጨረታው መከፈቻ ዕለት ተፈጻሚ በነበረው እና አሁን ያለውን ወቅታዊ ዋጋ አስመልክቶ በኤጀንሲው ወይም በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በተሰጠው ዋጋ መካከል ያለውን የዋጋ ልዩነት በማስላት ልዩነቱ በአቅራቢው ዋጋ ላይ እንዲጨመር ወይም እንዲቀነስ በማድረግ የሚቀጥለው የዋጋ ማስተካከያ ጊዜ እስከሚደርስ ድረስ የተስተካከለውን ዋጋ ተፈጻሚ ማድረግ እንዳለበት የተገለጸ ቢሆንም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ባልተሟላበት ሁኔታ በ2009 በጀት ዓመት ለ2008 ክረምትና 2009 የመደበኛ ተማሪዎች በማዕቀፍ በተፈጸመ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግልጽ ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግ ከአርባ ምንጭ ስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 24/05/09 በቁጥር 22-43/3/999 የወቅቱ የዋጋ ጥናት ዝርዝር በሚል የ11 ዓይነት ዕቃዎች የአንድ ወቅት ዋጋ ተጠይቆ ቀርቦ እንዲሁም በዩኒቨርስቲው ባለሙያዎች ተጠና ብለው ባቀረቡት የ13 ዓይነት ዕቃዎች ዋጋ ጥናት በአምዩ አስተዳደር ካውንስል ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ቁጥር 22/2009 እንዲጸድቅ በማድረግ የዋጋ ማሻሻያ እንዲደረግ ተደርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት በድምሩ ብር **2,990,763.73** በብልጫ መከፈሉን ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ ቁጥር 7 ቀርቧል)

3.2.5.2. **ስጋት ፣**

ዩኒቨርሲቲው የመንግስት ደንብና መመሪያን ተግባራዊ ባለማድረጉ ተጠያቂነትም ከማስከተሉ ባሻገር የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፡፡ ለምዝበራም መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

3.2.5.3. **የማሻሻያ ሃሳብ፣**

ዩኒቨርስቲው በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ውሎችን ማስተዳደር አለበት፡፡ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያም በመንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ

ማድረግና ከመመሪያና ደንብ ውጭ በዋጋ ማስተካከያ ስም ወጪ የተደረገ ገንዘብ ብር 2,990,763.73 ለመንግስት ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

3.2.5.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ዩኒቨርሲቲው ቀደም ሲል የምግብ ጥሬ እቃ ግዥ ለአንድ አመት ውል በማስፈረም ግዥ በሚፈጽምበት ጊዜ በመካከሉ የገበያው ዋጋ በከፍተኛ ፍጥነት ስለሚንር መጀመሪያ ውል በተገባበት ዋጋ አቅራቢዎች ለማቅረብ ፍቃደኛ በመቸገራችን በ2009 ለመጀመሪ ጊዜ በማእቀፍ ግዥ ስምምነት መሰረት ለመፈፀም የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣትና ይህንኑ በውሉ ውስጥ በ6 ወር እንደሚታደስ ዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ የተጀመረ ከማእከላዊ ስታትሲቲክስ ዋጋው በሚሻሻልበት ወቅት የነበረው የተላከልን ሲሆን ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት የነበረው ዋጋ ግን የዘገየብን ማሻሻያ ወቅት የነበረው ዋጋ እያለ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመን ጎን ለጎን በአርባምንጭ ዙሪያ የሚገኙ ገበያዎች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ኦዲት ባለሙያዎችን ጨምሮ ከተለያዩ ክፍሎች በተውጣጣ ኮሚቴ በማዋቀር ዋጋው ሲታይ ከስታቲስቲክስ ከመጣው ዋጋ የገበያው ዋጋ አነስተኛ በመሆኑ ማኔጅመንቱ ዩኒቨርሲቲውን ከመጥቀም አንፃር የገበያ ዋጋውን እንደመነሻ በመጠቀም የተፈፀመ ሲሆን ለተጨማሪ ማነፃፀሪያ እንዲሆን የስታቲስቲክስ መ/ቤትም ጨረታው ሲከፈት የነበረውን ዋጋ እንዲሰጥ በድጋሜ ሲጠየቅ የገበያ ዋጋ በመጠቀማችን ለመስጠጥ ፍቃደኛ ባለመሆኑ የዋጋ ማሻሻያው በገበያ ጥናቱ መሰረት እንዲሆን የተደረገ ቢሆንም ይኸው ችግር በ2010 እንዳይገጥመን በመመሪያው መሰረት ጨረታው ሲከፈትና አቅርቦቱ ሲጀምር የነበረው የስታቲስቲክስ ዋጋ እንዲሁም ዋጋው በሚሻሻልበት የነበረውን የስታቲስቲክስ ዋጋ በማስመጣት በግዥ ማኑዋሉ ላይ በተመለከተው የአሠራር ፎርሙላ መሰረት አርመን እየሰራን በመሆኑ በኦዲት በማሻሻያው ላይ የተመለከተው ለነጋዴው የተከፈለውን ገንዘብ ማስመለስ ግን እጅግ ከባድ በመሆኑ ከስህተታችን መታረማችን ታይቶ ውሳኔው ላይ አስተያየት ቢደረግልን፡፡

3.2.6 <u>በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ሲፈጸም አነስተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ያልተፈጸመ ግዥን ይመለከታል</u>።

3.2.6.1 <u>ግኝት</u>

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በዋጋ ማወዳደሪያ በተፈጸመ ግዥ አነስተኛ ዋጋ ካቀረበው እፍራታ የጽፈት መሳሪያ መፈጸም ሲገባው ሰስፔንሽን ፋይል ዋጋው ከነቫቱ ብር

14.40፣ የማዕተም ቀለም ከነቫቱ ብር 8.50 እና አቃፊ ባለ ብረት ከነቫቱ ብር 32.50 ያቀረበ ቢሆንም ከቫት በፊት እንዳቀረበ በመቁጠር ከሌላኛው አቅራቢ ከኃይለየሱስ ጋሻው የጽህፈት መሳሪያ ሰስፔንሽን ፋይል ከቫት በፊት ብር 13.89 እንዲሁም የማህተም ቀለም ከቫት በፊት ብር 8.00 እና አቃፊ ባለ ብረት ከቫት በፊት ብር 30.00 ግዥው በመፈጸሙ መንግስት ብር 6,063.00 ሊያጣ ችሏል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 9 ቀርቧል)

3.2.6.2 <u>ስጋት</u>

ዩኒቨርሲቲው በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ባለማድረጉ የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፡፡ ለምዝበራም መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

3.2.6.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

ዩኒቨርስቲው በቀጣይ የዋጋ ማነጻጸሪያ በሚሰራበት ወቅት የቀረበው ዋጋ የተ.እ.ታ. ማካተቱን ወይንም ያለማካተቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለቀጣይ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ማናጅመንቱም የእርምት ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

3.2.6.4 <u>የሚመለከተው አካል ምላሽ</u>

<u>በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከፋይናንስና በጀት ቡድን መሪ የተሰጠ ምላሽ</u>

እንደ ኢንስቲትዩት በዋጋ ማቅረቢያ ዘዴ ግዥ ሲፈፀም በመጀመሪያ የገበያ ዋጋ ጥናት ተደርጎ፣ አገልግሎቱ በተጠየቀበት ዘርፍ ላሉ አቅራቢዎች ፕሮፎርማ ተበትኖ ከተሰበሰበ በኋላ በፕሮፎርማ ከፋች ኮሚቴ ታይቶ ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢው ተለይቶ ለግዥ ንዑስ ሥራ ሂደት መሪ ይቀርባል፡፡ የግዥ ንዑስ ሥራ ሂደት መሪም ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ለማፅደቅ ለማኔጅንግ ዳ/ር ይቀርባል፡፡ በማኔጅንግ ዳይሬክተርም ተገቢው ፍተሻ ተደርጎ ችግር ከሌለ ይፀድቃል፡፡ ነገር ግን በሪፖርቱ የተገለፀውን የስቴሽኔሪ ግዥ ስንፈትሽ ከአቅራቢዎች መካከል አንዱ (ኤፍራታ የፅህፈት መሳሪያ) በዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ የ15% ቫት መረጃ ሳያካትቱ የሰጠ ሲሆን በግዥ መመሪያ መሠረት አቅራቢዎች ቫት ሳያካትቱ ዋጋ ሲሰጡ የግዥ ባለሙያዎች የ15% ቫት በማንሳት ዝቅተኛ ዋጋ ማስገባት ስገባቸው እንዳለ የቀረበውን ዋጋ ዝቅተኛ አድርጎ መውሰዳቸው ትክክል እንዳይደለ ተረድተናል፡፡ ምናልባትም የዚህ ዓይነት የአሠራር ክፍተት በግዥ ባለሙያዎች የልምድና ዕውቀት ማነስ የተፈጠረ ሊሆን ስለሚችል በቀጣይ ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይፈጠር ልዩ ጥንቃቄ ለማድረግና ለግዥ ባለሙያዎችም ተገቢውን ግንዛቤ ለመፍጠር ተግተን ለመሥራት

ያለውን ቁርጠኝነት እያሳወቅን በብልጫ የተከፈለውን ብር 6,063.00 (ስድስት ሺህ ስልሳ ሦስት ብር) በግዥ ሂደቱ ከተሳተፉ ባለሙያዎች ተቀራጭ ተደርጐ ለመንግሥት ካዜና ተመላሽ የምናደርግ መሆኑን ለመግለፅ እንወዳለን፡፡

3.2.7 <u>የጋራዥ አጥር ግንባታ ወቅት እስፔስፊክሽኑ ላይ የቆርቆሮ ዋጋ እንዳይካተት በተገለፀበት ሁኔታ የቆርቆሮውን ዋጋ ውሉ ላይ በማካተት ክፍያ መከፈልን ይመለከታል</u>፡፡

3.2.7.1 <u>ግኝት</u>

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ውሎች የሚዘጋጁት በቀረበው ጨረታ ሰነድ ላይ ባለው ዝርዝር ስምምነት መመሪያ (Specification) እንዲሁም ክፍያዎች የሚፈጸሙት በተገባው ውልና የዕቃዎች ዋጋ (bill of quantity) መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፡- በዩኒቨርስቲው በዋናው ግቢ የሚገኘውን የጋራዥ ዙሪያ አጥር የግንባታ ስራ ለማሰራት በወጣ የአካባቢ ጨረታ ይበልጣል ኮንስትራክሽን ማህበር በቀን 05/12/2008 በቁጥር አምዩ4/7/130 አሸናፊ መሆኑ ተገልጾ ውል የተገባ ሲሆን ሆኖም ግን ውሉ በቀን 16 ህዳር 2008 በቁጥር አምዩ5/6/65 በይዞታ ልማት መ/መ/ዳ/ጽ/ቤት በቀረበው ስፔስፊኬሽኑ (Specification and bill of quantity) ላይ እንደተጠቀሰው ቆርቆሮ በሳይት እንደሚገኝ ወይም በዩኒቨርስቲው እንደሚቀርብና የቆርቆሮ ዋጋ ብር 112,700.00 ከነቫቱ ወጪ እንደማይካተት (corrugated iron sheet 28 guage available at site, hence their costs are excluded) በተገለፀው መሰረት ሳይሆን የጋራዥ ዙሪያ አጥር ሙሉ ለሙሉ ግብዓቶችን በማቅረብ ለመገንባት በሚል ውል ተገብቶ ከዚህ በታች በቀረቡት የወጪ ማስመስከሪያዎች የቆርቆሮን ዋጋ በማካተት ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡-

| ተ.ቁ | ቀን | የወጪ ማስመስከሪያ | ብር ከነቫቱ |
|---|---|---|---|
| 1 | 30/12/08 | 941550 | 146,778.50 |
| 2 | 30/02/09 | 941857 | 146,778.50 |
| 3 | 30/09/09 | 944030 | 195,704.60 |
| | | ጠቅላላ ድምር | 489,261.60 |

### 3.2.7.2 ስጋት

የመንግስትን ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ያላደረገ አሰራር የመንግስት ሀብት ለብክነትና ለምዝበራ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

### 3.2.7.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

በዩኒቨርስቲው የሚዘጋጁ ውሎች የጨረታ ሰነድ ስፔስፊኬሽ መሰረት ያደረጉ መሆን አለባቸው እንዲሁም ማቴሪያል ኮስት በሚል የተፈጸመውን የቆርቆሮ ዋጋ ብር 112,700.00 ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል:: በተጨማሪ ማኔጅመንቱ ተመሳሳይ የሆኑ ሁኔታዎች እንዳይፈጸሙ ጥንቃቄ በማድረግ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

### 3.2.7.4 የሚመለከተው አካል ምላሽ

በጨረታ ሰነዱ ላይ ቆርቆሮ ከዩኒቨርሲቲው በኩል እንደሚቀርብ ቢገለጽም በሌላ መልኩ ደግሞ ለቆርቆሮ ዋጋ መሙያ ቦታ በመዘጋጀቱና ሁሉም ተወዳዳሪ ማህበራትም ቆርቆሮ ዋጋ በሚለው ቦታ ክፍት በማድረግ ሲገባቸው ሞልተው መወዳደራቸውና የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴመ ዝርዝር የተሞላውን ሳይመለከቱ ደምረው በማቅረብ እንዲፀድቅ በመደረጉና ግንባታውን የሚያሰራው ይዞታ ልማት መገ/መሳ/አስ/ዳይሬክቶሬትም ይህንኑ ሳያጣራ የክፍያ ሰርተፍኬት በማዘጋጀት ለግ/ን/አስ/ዳይሬክተር በመላኩ ለማህበሩ ያለተገባ በገንዘብምና በአይነት ክፍያው እንዲፈፀም የተደረገ ቢሆንም ጉዳዩ እንደታወቀ የግዥ አገልግሎትሃ ንብረት አስተዳዳር ዳይደሬክተር ጽ/ቤት በማጭበርበር ገንዘቡን ለወስደው ግንባታ ድርጅት ማህበር አለአግባብ የወሰደውን ገንዘብ በአስገዃይ ገቢ እንዲያደርግ በቁጥር አ ምዩ 6/17/74 በቀን 23/4/2010 የተፃፈ ደብዳቤ እንደደረሰን በማድረግና በማያያዝ ጨረታውን በገመገሙት የግዥ ሰራተኞች ላይ ጉዳዩ ተጣርቶ አጥፊው በህግ እንዲጠየቅ በቁጥር አምዩ6/17/83 በቀን 24/4/2010 ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የገለጽን ሲሆን ፕሮዚዳንት ጽ/ቤትም ተጣርቶ በአጥፊዎች ላይ ክስ እንዲመሰረት ለአስተዳደር ጉዳዩች ተመርቶ ጉዳዩ እየታየ ይገኛል፡፡ ስለዚህ አቅራቢው በተፃፈለት ደብደቤ መሠረት የግንባታ በማህበሩ ገንዘቡን በተያዘለት ጊዜ ገደብ ውስጥ መመለሰ ባለመቻሉ ድርጅቱ ላይ ክስ እንዲመሰረት ከግ/ን/አስ/ዳይሬክተር ጽ/ቤት በቁጥር አምዩ 6/17/130 በቀን 15/5/2010 በተፃፈ ደብደቤ ለፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ቀርቦ በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

### 3.2.8 በአንድ ሰነድ ሁለት ጊዜ ተወራረዶ የተገኘ ሂሳብ፡፡

#### 3.2.9.1 ግኝት

የወጪ ሂሳቦች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት በሕጋዊ የክፍያ ማስረጃ የተደገፉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ስናከናውን፣ ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13404 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54993 ብር 333,210.95 በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቀርቦ የተወራረደ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚሁ አገልግሎት በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 941435 ብር 333,210.95 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ መገኘቱን፣ ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13406 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54963 ብር 45,489.42 በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቀርቦ የተወራረደ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚሁ አገልግሎት በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 941591 ብር 45,489.42 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ መገኘቱን፣ ለኢትዮ ኒፖን የቴክኒክ ማህበር ለሰ.ቁ ኮድ 4-13405 መኪና ጥገና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 91480 ብር 84,284.19 በገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ቀርቦ የተወራረደ ሲሆን በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚሁ አገልግሎት በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 941561 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ መገኘቱን፣ በድምሩ ብር **462,984.56** በአንድ በተመሳሳይ ሰነድ ሁለት ጊዜ አለአግባብ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 10 ቀርቧል)

#### 3.2.9.2 ስጋት

የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር በአግባቡ ተግባራዊ የማይደረግና ተፈጻሚነቱም የማይገመገም ከሆነ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

#### 3.2.9.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ያለአግባብ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ የተገኘውን ብር **462,984.56** ተመላሽ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል:; በተጨማሪም ይህ ሰነድ እንዲወራረድ ባደረጉ ሰራተኞች ላይ የዩኒቨርስቲው አስተዳደር አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል::

#### 3.2.9.4 የስራ አመራሩ ምላሽ

ይህ የሆነው በሂሳብ ምዝገባ ወቅት አዳዲስ ባለሙያዎች በስራ መደቡ ላይ በመመደባቸው ከጥንቃቄ ማነስ የተፈፀመ ስለሆነ በቀጣይ የሂሳብ አሰራሩን በሂሳብ ምዝገባ ስርአት የምናስተካክል ስለሆነ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት የምንፈፅም መሆኑን እንገልፃለን ::

## 3.2.10 አሮጌ የመኪና መለዋወጫ በአዲሱ ሲተካ ለአሮጌው እቃ ገቢ ለመሆኑ የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ያልቀረበለት ስለመሆኑ፤

### 3.2.10.1 ግኝት ፤

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ 9/2003 አንቀጽ 16 ቁጥር 2 በመለዋወጫነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም እንዲሸጡ ከተወሰነባቸው ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች ላይ ጠቃሚ አካሎችን ፈቶ አግባብ ባለው የእቃ አስተዳደር መሰረት ገቢ እንዲሆኑና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ወይም በጨረታ እንዲሸጡ ማድረግ እንደሚቻል ይገልጻል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በተገለጸው መሰረት ስለመስራቱ ሲረጋገጥ፣ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር 3,206,776.65 የመኪና መለዋወጫ እቃ ገዝቶ ሲቀይር የተቀየረው አሮጌ የመለዋወጫ እቃ ወደ ዩኒቨርስቲው ንብረት ክፍል ገቢ ለመደረጉ የአሮጌ እቃ ገቢ ደረሰኝ ከወጪ ሰነዱ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩን በአባሪ ቁጥር 11 ቀርቧል)

### 3.2.10.2 ስጋት ፤

አሮጌ የመኪና መለዋወጫ በአዲሱ ሲተካ አሮጌዉ በአግባቡ ገቢ የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ንብረት ለብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 3.2.10.3 የማሻሻያ ሃሳብ፣

የዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ የመለዋወጫ እቃ ክፍያ ሲፈጽም አሮጌ እቃው በእቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ገቢ ሆኖ መቅረቡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

### 3.2.10.4 የሚመለከተው አካል ምላሽ

የአሮጌ ዕቃ ገቢ ማድረግያ በሞዴል 19 ገቢ መሆኑ ከክፍያ በኃላ የሚመጣ መረጃ በመሆኑ የተፈፀመ እንደሆነ እየገለጽን ተመላሽ እቃዎች በሞዴል 19 ገቢ የተደረጉ ቢሆንም ወደ ፋይናንስ ለክፍያ በማቅረብ ሂሳቡን ለማወራረድ የማቅረብ ልምዱ ጎልቶ ያልታየ ቢሆንም በቀጣይ አያይዘን የምናሳይና አሰራሩንም በኦዲት አስተያየቱ መሰረት አሻሽለን የምንቀጥል መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

## 3.3 ሂሳብ መደቡን ያልጠበቀ ክፍያ ፤

### 3.3.1. ግኝት ፤

የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥራዝ 2 የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ተመዝግበው ሪፖርት መደረግ እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት ለመከናወኑ ኦዲት ሲደረግ፣ በዋና ግቢ በድምሩ ብር

74,626,574.31 የተለያዩ የወጪ ሂሳብ መደቦች ትክክለኛውን የሂሳብ መደባቸውን ጠብቀው ያልተመዘገቡ መሆኑን በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ 12 ቀርቧል)

3.3.2. ስጋት፣

ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ አርዕስት ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የዩኒቨርሲቲውን የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ እንዳያሳይ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡

3.3.3. የማሻሻያ ሃሳብ ፣

የወጪዎች ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክክለኛ የወጪ ሂሳብ አርዕስታቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያደርስ በመሆኑ ወጪዎች የሚመዘገቡት በትክክለኛው የበጀት አርዕስታቸው ለመሆኑ ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡ በመሆኑም ለተፈጠረው ስህተት ተገቢውን ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

3.3.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ይህ የሆነው ቀደም ሲል በተደረጉ የኦዲት አስተያየቶችን መሠረት በማድረግና አንዳንድ ተመሳሳይነት ባህሪ ባላቸው የወጪ ኮዶች ላይ ትዕዛዝ ሲተላለፍ ግልፅ ሆኖ ባለመጠቀሱ ምክንያት የበጀት ሁኔታ ለማጣጣም ሲባል የተደረገ ስለሆነ በቀጣይ የሚስተካከል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

3.4. በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ሂሳብ፣

3.4.1. ግኝት፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስከጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም እንደማይገባ መመሪያው ይገልፃል፡፡ በዚህም መሠረት በዩኒቨርሲቲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በዩኒቨርሲቲው ለተፈፀሙ የዕቃ እና የአገልግሎት ግዥዎች፣

በዋናው ግቢ በድምሩ ብር 3,091,874.79 ለ2008 በጀት ዓመት ለተፈጸመ ግዥና ለዋለ አገልግሎት በበጀት እጥረት ምክንያት ሳይከፈል የቀረ በማለት በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | ቀን | የወጪ ማስመስከሪ ቁጥር | የወጪው ምክንያት | የእቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ቁጥር/ሞ-19/ | እቃው ገቢ የሆነበት ቀን | የሂሳብ መደብ | የገንዘቡ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 25/05/09 | 198793 | ለአራት ስፖርት አካዳሚ አሰልጣኞች የ2008 በጀት አመት ክፍያ | - | - | 6116 | 23,076.00 |
| 2 | 30/30/09 | 0704179 | የ2008 ዓ.ም የሰራተኞች የደንብ [illegible] | - | - | 6211 | 311,940.00 |
| 3 | 28/04/09 | 0704510 | ‹‹ ›› | - | - | ‹‹ ›› | 161,090.00 |
| 4 | 30/06/09 | 0704997 | ‹‹ ›› | - | - | ‹‹ ›› | 128,065.00 |
| 5 | 30/03/09 | 0704170 | ‹‹ ›› | - | - | ‹‹ ›› | 135,245.00 |
| 6 | 30/03/09 | 0704180 | ‹‹ ›› | - | - | ‹‹ ›› | 159,690.00 |
| 7 | 28/04/09 | 0704509 | ‹‹ ›› | - | - | ‹‹ ›› | 320,040.00 |
| 8 | 29/11/08 | 941351 | Auto Transformer direct on line 30kw board | 0045396 | 30/10/08 | 6324 | 742,900.00 |
| 9 | 30/11/08 | 941359 | ድፍን አተር | 0047044 | 02/10/08 | 6216 | 101,220.00 |
| | | | | | | ድምር | **3,091,874.79** |

3.4.2. **ስጋት፣**

- በ2008 በጀት ዓመት የተከናወኑ ስራዎች በ2009 በጀት ዓመት ወጪውን መፈጸም በበጀት ዓመቱ በዕቅድ በተያዙ ስራዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥራል፡፡
- ክፍያዎች በጀት ዓመታቸውን ጠብቀው ካልተመዘገቡና ሪፖርት ካልተደረጉ የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ ምክንያት ይሆናሉ፡፡

### 3.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ ፣

በ2009 በጀት ዓመት በዕቅድ ለተያዙ ስራዎች ማከናወኛ ከተፈቀደለት በጀት የቀድሞውን በጀት ዓመት ክፍያ መፈጸሙ ተቋሙ የበጀት ህጉን ተከትሎ አለማከናወኑን ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ክፍያዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ እና ተገቢው የበጀት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ እንዲደረግ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል ፡፡

### 3.4.4. የሚመለከተው አካል ምላሽ

ይህ የሆነው በበጀት አመቱ የግዥ እቅድ ውስጥ ያልተካተቱና ለትምህርት ወሳኝ የሆኑ እቃዎች በበጀት አመቱ መጨረሻ አካባቢ በመታወቃቸውና ግዥ ተጠይቆ በግዥ አሰራር ሂደት ላይ ሆነው ነገር ግን በበጀት አመቱ ውስጥ አልቀው ክፍያ መፈፀም ሲገባው ሳይደርሱ የቀሩት በክፍያ ውል አስገዳጅነት መሰረት በማነጅመንት እውቅና ተወስኖ የተፈፀሙ መሁኑን እንገልፃለን፡፡

## 3.5. በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተወራርዶ የተገኙ ሂሳቦች

### 3.5.1. የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የተወራረደ ሂሳብ

#### 3.5.1.1. ግኝት

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ተቋማት አገልግሎት ለተፈፀሙ ክፍያዎች ተገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለኩይሌ እንጨትና ብረታ ብረት ኢንተርፕራይዝ የተደራራቢ አልጋና ባለእጀታ ወንበር ጥገና እና ግዥ በቀጥታ ሲከናወን ብር 1,066,699.75 የተፈጸመ ቢሆንም የቀረበው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የብር 756,686.55 ሲሆን በልዩነት ለብር 310,013.26 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲሁም ባንክ ዴቢት አድቫይስ ሳይቀርብ ተወራርዶ መገኘቱን፣
- በነጭ ሳር ካምፓስ በቀን 02/07/09 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 347673 በሂሳብ መደብ 6212 ለኡስማን ሀሰን የጽህፈት መሳሪያ መሸጫ መደብር የሳይት ቦርድ፣ሰስፔንሽን ፋይልና መዝገብ ግዥ ብር 55,200.00፣ በቀን 01/06/09 የባንክ

ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 347534 በሂሳብ መደብ 6215 ለወ/ሮ የሺ መሐመድ(አርባ ምንጭ ስፖርት እቃዎች መሸጫ) የእስፖርት ትጥቅ ግዥ ብር 64,112.15፣ በቀን 02/09/09 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 920496 በሂሳብ መደብ 6212 ለኡስማን ሀሰን የጽህፈት መሳሪያ መሸጫ መደብር የጽህፈት መሳሪያ እቃዎች ግዥ ብር 43,481.50 እና በቀን 23/10/09 የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 920734 በሂሳብ መደብ 6218 ለኡስማን ሀሰን ኢንተርፕራይዝ የጽዳት እቃዎች ግዥ ብር 89,125.00፣ በድምሩ ብር 251,918.65 ለተከፈለ ክፍያ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳያቀርብ በካሽ ሴልስ ኢንቮይስ አታችመንት(አባሪ) ክፍያ መፈፀሙን፣ በአጠቃላይ ድምር ብር **561,931.91** የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሳያቀርብ ክፍያ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡

3.5.1.2. ስጋት

የወጪ ሂሳብ ህጋዊ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተመዝግቦ ሪፖርት መደረጉ የመንግሥትን ገንዘብ ለብክነት ይዳርጋል፣ ተጠያቂነትንም ያስከትላል፡፡

3.5.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ተወራርዶ ለተገኘው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ እንዲመለስ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

3.5.1.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ማስረጃ ያልቀረበላቸውን ከአቅራቢዎቹ በቀጣይ በመሰብሰብ የምናቀርብ ይሆናል ፡፡

3.5.2 በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተወራረዱ ሂሳቦች

3.5.2.1. ግኝት

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው ደረሰኝ መሆን እንዳለበት መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ተቋማት አገልግሎት ለተፈፀሙ ክፍያዎች ተገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በዋናው ግቢ በድምሩ ብር **4,493,020.81** ለዕቃና ለአገልግሎት ግዥ በተፈፀመ ክፍያ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 13 ቀርቧል)

#### 3.5.2.2. ስጋት

- በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሂሳብ ማወራረድና መመዝገብ ሂሳቡ በድጋሚ ክፍያ ሊጠየቅበት የሚችልበትን ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከድርጅቶቹ ለሚፈለግ የመንግስት ግብርና ታክስ ክትትልና ቁጥጥር አመቺ አይደለም፡፡

#### 3.5.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ

- ለወጪ ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ ሂሳቡ እንዳይወራረድ እና እንዳይመዘገብ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለተጠቀሰውም ሂሳብ ከድርጅቶቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊቀርብለት ይገባል፡፡

#### 3.5.2.4. የስራአመራሩ ምላሽ

ይህም የሆነው ገንዘብ ቀድሞ ከመተላለፉ በፊት ድርጅቶቹ በራሳቸው አሠራር በዩኒቨርሲቲው ላይ ዕዳ እንዳለበት የሚገልፁበትን የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ ሲያቀርቡ ሌሎች ተገቢ ማስረጃዎች መሟላታቸው ተረጋግጦ ገንዘቡ ከተላለፈ በኃላ የገንዘብ ገቢ ደረሰኝ የሚሰጡበት አሠራር እየተገበረ የሚገኝ ሲሆን እኛም  ደረሰኝ በመያዝ የገቢ ደረሰኞችን ከድርጅቶች ስናገኝ የምንሰጣቸው ስለሆነ በአንዳንድ ምክንያቶች ያልተያዙትን ደረሰኞች ከድርጅቶቹ ወስደን የምናያይዘው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

### 3.5.3. የሂሳብ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተወራርዶ የተገኘ ሂሳብ

#### 3.5.3.1. ግኝት

ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊትም ሆነ ቀድመው ለተከፈሉ ክፍያዎች ከመወራረዳቸው በፊት በቂ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ በናሙና ከተመረጡት ክፍያዎች እና ማስተካከያዎች ውስጥ

በዋናው ግቢ

- በቀን 30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 91650 ብር 807,039.96፣ በ91848 ብር 780,008.50፣ በ89150 ብር 997,543.56፣ በ91642 ብር 401,067.93 በድምሩ ብር 2,985,659.95 ምንም አይነት ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳብ መወራረዱን፣
- በቀን 23/09/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 91472 ለሞኤንኮ  የመኪና ሰሌዳ ቁ.11927 ጥገና ብር 387,906.32 ወጪ የተደረገ ሲሆን ለብር 374,461.91 ማስረጃ ቀርቦ ሲወራረድ በልዩነት ለብር 13,444.41 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብና በተሰብሳቢም ሳይመዘገብ ተወራርዶ መገኘቱን፣

- በቀን 30/10/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 89135 ለኒያላ ሞተርስ አ.ማ. የመኪና እቃ መለዋወጫ ግዥ ብር 89,712.14 ወጪ የተደረገ ሲሆን ለብር 78,712.14 ማስረጃ ቀርቦ ሲወራረድ በልዩነት ለብር 11,222.18 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብና በተሰብሳቢም ሳይመዘገብ የተወራረደ መሆኑን፣
- ቀን 28/04/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0704496 ተማሪዎች ከሆስፒታል ህክምና ያገኙበት ለአርባ ምንጭ ሆስፒታል ተማሪዎቹ ከሆስፒታሉ አገልግሎቱ ስለማግኘታቸው ማስረጃ፣ ፊርማ የተላኩበት ሰነድ ባልቀረቡበት ሁኔታ ክፍያ ብር 56,102.34 መፈፀሙን፣ በጠቅላላ ድምር **3,066,428.88** በቂ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተወራርዶ ተገኝቷል፡፡

### 3.5.3.2 ስጋት

የመንግስትን ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ያላደረገ አሰራር የመንግስት ሀብት ለብክነትና ለምዝበራ ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

### 3.5.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች ከመወራረዳቸው በፊት በቂ ማስረጃ መቅረቡን መረጋገጥ አለበት፤ በተጨማሪ ያለማስረጃ ተወራርዶ የተገኘውን ብር **3,066,428.88** በተሰብሳቢ በመመዝገብ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል።

### 3.5.3.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ምንም አይነት ማስረጃ ሳይቀርብ ለተወራረደው በቀጣይ አሟልተን የምናሳይ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- ይህ የሆነው ገንዘብ ወደ ካምፓኒዎች ከተላለፈ በኃላ በመኪናዎች ላይ በስፔር ፓርት (እቃ እጥረት) ተከስተው ወይም እቃው ተጠይቆ ነገርግን የነበረው እቃ የሚሰራ ሲሆን ሂሳቡ ተቀንሶ ከተገለፀ በኃላ የሚመለከታቸው የግዥ ሰራተኞችና የሂሳብ ሰራተኞች ተናበው ከካምፓኒው ተመላሽ ገንዘብ ያደረጉበትን ሰነድ ሳያያይዙ የተፈፀሙ ስለሆነ በቀጣይ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት የምናስተካክል መሆኑን እንገልፃለን ፡፡
- ይህ የሆነው የህክምና አገልግሎቱን የሚያገኙ ካምፓሶች በሚሰጡት ማረጋገጫ መሰረት ሆስፒታሉ ጥያቄ ሲያቀርብ የሚፈፀም ስለነበር በቀጣይ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሚፈፀም መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

### 3.5.4. የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ሂሳብ፣

#### 3.5.4.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 3 ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል 19/ ተቆርጦ መያያዝ እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0704133 እና 943547 በድምሩ ብር 292,692.00 ከኃይለ ጊዮርጊስ እርገጤ የመፅሔትና የጋዜጦች መሸጫ መደብር የህትመት ግዥ እና በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 55556 ብር 57,500.00 ከሳምኬት ኃ/የተ/የግ/ማ የቁልፍ መያዣ ግዥ በአጠቃላይ ድምር ብር 350,192.00 ክፍያ ሲፈፅም ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተያየዘ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል ::

#### 3.5.4.2. ስጋት

ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ላልተደረገና ዩኒቨርሲቲው ጥቅም ላላገኘበት ንብረት ገንዘብ ተከፍሎ ሊሆን ይችላል፡፡

#### 3.5.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ንብረቶቹ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ተደርገው ወይሞ ዩኒቨርሲቲው በንብረቶቹ ተጠቅሞ ከሆነ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ወይም ደረሰኙን ሊተካ የሚችል ማረጋገጫ ሊቀርብ የሚገባ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

#### 3.5.4.4. የስራ አመራሩ ምላሽ

ይህ የሆነው ከዚህ ቀደም ሲል በህትመት የሚቀርቡት በአብዛኛ በዚህ አሠራር ሳይሆን ያቀረቡት መጠን ትክክለኛ ሲረጋገጥ ብቻ እየተፈፀመ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በኃላ በተጠቆመው መሠረት የምናከናውን ይሆናል፡፡

### 3.5.5. በኮፒ ሰነድ የተወራረደ ሂሳብ

#### 3.5.5.1. ግኝት

የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ቁጥር 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባ ጥንቃቄዎች ንዑስ ቁጥር 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ሲወራረድ በማስረጃነት የቀረበው ኦሪጂናል ደረሰኝ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በዋናው ግቢ በቀን 29/07/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0705175 ለኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ አገልግሎት ግዥ ብር 216,287.47 ለኢትዮጲያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ደቡብ ሪጅን ክፍያ ሲፈፅም የክፍያ ማስረጃ ኮፒ መሆኑ፣
- በአባያ ካምፓስ በቀን 14/10/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 939207 ለጽዳት እቃዎች ግዥ ብር 49,606.00 ለኡስማን ሀሰን የንጽህና እቃዎችና የጽህፈት መሳሪያ መሸጫ መደብር ክፍያ ሲፈፅም የክፍያ ማስረጃው ኮፒ ከመሆኑም በተጨማሪ በካሽ ሴልስ አታችመንት ተወራርዶ መገኘቱ፣ በድምሩ ብር 265,893.47 ከባንክ የወጪ ማስመስከሪያው ጋር የተያያዘው የክፍያ ማስረጃ ኮፒ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.5.5.2. <u>ስጋት</u>

የክፍያ ማስረጃው ከሌላ ሰነድ ጋር ተያይዞ በድጋሚ ክፍያ ሊፈጸምበት ይችላል።

3.5.5.3. <u>የማሻያ ሃሳብ</u>

ገንዘብ ወጪ ከመደረጉ አስቀድሞ ክፍያዎች ለክፍያ የሚቀርቡ ማስረጃዎች ኦሪጅናል መሆናቸውን ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ኦሪጅናል ሰነዱ ከባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ጋር መያያዝ አለበት፡፡

3.5.5.4. <u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ይህ የሆነው ድርጅቱ የመንግሥት ተቋም ከመሆኑ አንፃር ክፍያው የተላለፈ ቢሆንም ደረሰኝ ሲጠየቅ ዋናውን በጥንቃቄ ባለማስቀመጣቸው የነበረበት ባለማስታወስ ኮፒ የተሰጠን ስለሆነና በኦርጂናሉ ሌላ የተላለፈ ገንዘብ የሌለ ስለሆነ የባንክ አድቫይስ በማቅረብና ኦርጅናሉን በደብዳቤ መ/ቤቱን በመጠየቅ ተገቢ ምላሽ ጋር የምናያይዝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
- አቶ ኡስማን ሀሰን የንጽህና እቃዎችን ለአባያ ካምፓስ ጨረታ ማሸነፉ ተገልጾለት ንብረቶቹን በሞዴል 19 ገቢ ካደረጉ ቡኃላ ክፍያ እንድንፈጽም ለፋይናንስ የትእዛዝ ደብዳቤ ተጽፎ ፋይናንስም በቀረበለት ሰነድ መሰረት ክፍያውን አዘጋጅቶ ወጪ መክፈያና ቼክም ተፈርሞ ካለቀ ወዲህ ሰነዱ ለጊዜው የተቀመጠበት ቦታ በመሰወሩ ምክንያት ባለመብቱ ክፍያ እየጠየቁን የቆየ ቢሆንም የበጀት ዓመት ከመጠናቀቁ እና ባለመብቱን ከማጉላላት ብለን ክፍያውን የፈፀምን ሲሆን ንብረቱ ገቢ የሆነበት ሞዴል 19 በንብረት ክፍሉ

ውስጥ ፓድ የሚገኝ መሆኑን እየገለፅን ሰነዱን እየፈለግን እንደምንገኝ እናሳውቃለን::

## 3.6. ካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎችን ሂሳብ በተመለከተ

### 3.6.1 ግኝት

በ2009 በጀት ዓመት በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ኮሌጆችና ዲፓርትመንቶች የካፌ ተጠቃሚና ተጠቃሚ ያልሆኑ ተመሪዎች ዝርዝር ለተማሪዎች አገልግሎት ተጠይቆ በቁጥር SSC/42/582/10 በቀን 25/03/10 በቀረበው መረጃ መሰረት የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች የህዳር፣ የታህሳስ እና የየካቲት ወራት 2009 በልዩነት ብዛት በቁጥር 409 ተማሪዎች በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ቀርቧል፡

| የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር | ወር | ክፍያ የተፈጸመላቸው ካፌ የማይጠቀሙ ተማሪዎች ብዛት | ከተማሪዎች አገልግሎት ካፌ የማይጠቀሙ ተማሪዎች ብዛት | የተከፈለ የገንዘብ መጠን | በብልጫ የተከፈላቸው ተማሪዎች ብዛት | በብልጫ የተከፈለ የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 55239 | ህዳር | 1,507 | 1,498 | 678,150.00 | 9 | 4,050.00 |
| 55590 | ታህሳስ | 1,585 | 1,537 | 713,250.00 | 48 | 21,600.00 |
| 91462 | የካቲት | 1,916 | 1,564 | 838,290.00 | 352 | 154,007.00 |
| | | | ጠቅላላ ድምር | **2,229,690.00** | **409** | **179,657.00** |

### 3.6.2. ስጋት

ክፍያዎች ከሚመለከተው አካል በሚቀርብ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ክፍያዎች የማይፈጸሙ ከሆነ የመንግሥትን ሀብት ለብክነት መንገድ የሚከፍት ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

### 3.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ዩኒቨርሲቲው የካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች ከተማሪዎች አገልግሎት በቀረበው መረጃ መሰረት ተጣርቶ በብልጫ የተከፈሉ ክፍያዎች ተመላሽ መደረግ አለበት ፡፡ ለቀጣይ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ማናጅመንቱም የእርምት ርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

3.6.4. <u>የስራአመራሩ ምላሽ</u>

የካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች ክፍያ በየካምፓሱ ተጠርተውና በተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በኩል ክፍያ ታዘው የሚቀርብልን ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የተማሪዎች ብዛት መረጃ በትክክል ሳይጣራ ነገር ግን ተማሪዎች የካፌ ተጠቃሚ ያልሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የካፌ ተጠቃሚ ተማሪዎች መቆጣጠሪያ ሥርዓት ያለው አሰራርን እየተከተሉ የሚሰራበት አግባብ ያለ ስለሆነ ለወደፊቱ ይህን ሆኔታ በኦዲት ግኝቱ መሠረት አጣርተን እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 3.7. <u>በሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የሂሳብ ምዝገባ</u>

3.7.1 <u>ግኝት</u>

የዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት ሂሳብ አያያዝ አንቀጽ 6 ተ.ቁ.6 ፊደል (ለ) የሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻ ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሂሣቦች በእለቱ በፋይናንስ ምንጩ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረሱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ዋና ግቢ በናሙና ከተመረጡት ክፍያዎች ውስጥ

- በቀን 30/12/08 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 941549 ደሳለኝ ዳካ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የጎርፍ መከላከያ ስራ ላከናወነበት የተፈጸመ ክፍያ ብር 94,221.09፣
- በቀን 30/10/09 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 941269 ውበት አርባ ምንጭ ሕ/ስራ/ማህበር የተማሪዎች ዳቦ ግዥ የተፈጸመ ክፍያ ብር 221,536.74፣
- በቀን 30/07/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 55351 የአባያ ካምፓስ የመጋቢት ወር የ ተማሪዎች የተፈጸመ ክፍያ ብር 215,100.00 እና
- በቀን 28/04/09 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 54996 ለደቡብ ኦሞ ምርምር ማዕከል ሙዚየም ዳ/ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ ለቲዎር አስመጪ ብር 185,050.03 በድምሩ ብር **715,907.86** ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም በ2009 በጀት ዓመት የሂሳብ ምዝገባ ሳይከናወን መገኘቱ ተረጋግጧል ፡፡

3.7.2. <u>ስጋት</u>

የመንግስትን ደንብና መመሪያ ተግባራዊ ያላደረገ የሂሳብ አሰራር የሂሳብ ሪፖርቱን የተዛባና ተዓማኒነት የጎደለው ያደርገዋል፡፡

### 3.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ ምዝገባቸው በወቅቱ ሊከናወን ይገባል፡፡

### 3.7.4. የስራአመራሩ ምላሽ

ይህ የሆነው በሂሳብ ምዝገባ ወቅት የተመዘገቡና ያልተመዘገቡ በትክክል አጣርተውና ምልክት አድርገው ከመለየት ችግር የመነጨ ስለሆነ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ በማስተካከል በኦዲት አስተያየቱ መሰረት የምንፈፅም መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 3.8. የግንባታ ሂሳብ ፣

### 3.8.1. በውል ጊዜያቸው መሰረት ባልተጠናቀቁ ግንባታዎች ላይ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያልሆነ የጉዳት ካሳን በተመለከተ፣

#### 3.8.1.1. ግኝት ፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/3 (ሸ) መሠረት ህንጻ ተቋራጩ በውሉ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ የግንባታ ዘርፍ ሥራውን አጠናቅቆ ባያስረክብ ላዘገየበት ጊዜ የሚወሰደውን እርምጃ በህንጻ ተቋራጩ እና በመንግሥት መ/ቤት መካከል በሚደረግ ውል መካተት እንዳለበት የተገለጸ ሲሆን በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 27/4/ሀ መሰረት ደግሞ ከፍ ሲል በመመሪያው አንቀጽ 16.27.3 (ሸ) መሠረት ሕንጻ ተቋራጮች ግዴታቸውን ባይወጡ ግዴታቸውን ሳይወጡ ለዘገዩበት ጊዜ ሳይፈጽሙ በቀረው የውል መጠን ላይ በየቀኑ 1/1000ኛ መቀጣት እንዳለባቸው እና በዚህ ዓይነት የሚታሰበው መቀጫ የውሉን 10% መብለጥ እንዳሌለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡በዚህ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፡-

- ፍሊንት ስቶን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.ግል.ማህበር በአባያ ካምፓስ የኮንፈረንስ አዳራሽ፣ ፋውንቴን እና የሳይት ስራ የውሉ መጠን ብር 200,315,729.00 በውሉ መሰረት የግንባታው ስራ የሚጠናቀቅበት የተፈቀደ የጊዜ ማራዘሚያን ጨምሮ 19/10/2005 ዓ.ም ቢሆንም እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም ርክክብ ያልተደረገ በመሆኑ ለዘገየበት 1472 ቀናት ሲሆን ግንባታው ያለበት ደረጃ 62.46% በመሆኑ በዚህም መሰረት አማካሪው አስልቶ ያቀረበው የቅጣት ብር መጠን ብር 15,677,585.83 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከስሌቱ እና ከውሳኔው በኋላ ተሰርተው ከቀረቡ የሥራ ተቋራጩ ክፍያ ላይ 6,304,647.74 + 1,252,258.13 = 7,556,905.87 ተቆርጦ

ለዩኒቨርሲቲው ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው የጉዳት ካሳ ከሚቀጥሉት ክፍያዎች የሚቀናነስ ይሆናል፡፡የጉዳት ካሳ ብር 8,120,679.96 የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ያላደረገ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3.8.1.2. <u>ስጋት</u> ፤

ውለታ የተገባባቸውና ከፍተኛ የካፒታል በጀት ወጪ የተደረገባቸው ግንባታዎች በወቅቱ አለመጠናቀቅ በተቋሙ የመማር ማስተማር (በተማሪዎች ቅበላ፣በተግባር ትምህርት አሠጣጥ) እና በሌሎችም አገልግሎቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በተጨማሪ በግንባታዎቹ ሥራ መጓተት ለሌላ የልማት ሥራ ሊውል የሚችለውን ከፍተኛ መጠን ያለው የቅድሚያ ክፍያ በተቋራጮቹ እጅ እንዲቆዩ እና ለሌላ ግንባታ እንዲያውሉት ዕድል ይሰጣል፡፡

3.8.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፤

የፕሮጀክት ማጠናቀቂያና የማስረከቢያ የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተጠናቀቁ ሥራዎች ተጠናቀው የተፈለገውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ እና መንግስት ላወጣው ወጪ ተመጣጣኙን እንዲያገኝ በገቡት ውለታ መሠረት ግዴታቸውን ባልተወጡ ተቋራጮች ላይ በዩኒቨርሲቲው ላይ ላደረሱት ጉዳትና ኪሳራ ሊጠየቁ ይገባል፡፡

3.8.1.4 <u>የስራ አመራረሩ ምላሽ</u>

ዩኒቨርሲቲው ከላይ በተገለፀው መሰረት አለአግባብ የውለታ ጊዜያቸውን ካሳለፉ ተቋራጮች ላይ በደንቡና መመሪያው መሰረት የጉዳት ካሳ እየቆረጠ ሲሆን በድምሩ 9,860,613.33 ብር ከፍሊንስቶን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ክፍያ ላይ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማድረጉን መግለጽ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት

- ፍሊንስቶን ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማህበር በአባይ ካምፓስ የኮንፍራስ አዳራሽ ፣ ፋውንቴን እና የሳይት ስራ ፕሮጅክትን በተመለከተ መጠናቀቅ በነበረበት ጊዜ ባለመጠናቀቁ ዩኒቨርሲቲው የጉዳት ካሳ እንዲቀጣ በወሰነው መሰረት ሥራውን እያማከረ የሚገኘው አማካሪ በውለታው አግባብ መሰረት መቀጣት ያለበትን የጉዳት ካሳ ስሌት በመመሪያው መሰረት አስልቶ እነዲያቀርብ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አማካሪው አስልቶ ያቀረበው የቅጣት ብር መጠን ብር 15,677,585.83 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ከስሌቱ እና ከውሳኔው በኋላ ተሰርተው ከቀረቡ የሥራ ተቋራጩ ክፍያ ላይ 6,304,647.74 + 1,252,258.13 = 7,556,905.87 ተቆርጦ

ለዩኒቨርሲቲው ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው የጉዳት ካሳ ከሚቀጥሉት ክፍያዎች የሚቀናነስ ይሆናል፡፡ለአስረጅነትም በአማካሪው በኩል ተሰልቶ የቀረበው ሰነድና የክፍያ ሰነዶች ተያይዟል፡፡

- ኤፍ ኢ ኮንስትራክሽንና አንጀሎ አርሼ ኮንስትራክሽንን የእንሰት ፓርክ እና የደጋ ፍራፍሬ ምርምር ማዕከል ግንባታ በሚመለከት አማካሪው በተለያዩ አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶች የውለታ ጊዜው የሚራዘምበት ሁኔታ ካለ የውለታ ማጠናቀቂያ ጊዜውን በመከለስ እንዲያቀርብ ከልሆኔ አሳማኝ ባልሆነ ምክንያቶች የባከኑ ጊዜያት ተለቅመው የጉዳት ከሳ አስልቶ ከቀጣዩ ክፍያዎች ቆርጦ እንዲያቀርብ ከዩኒቨርሲቲያችን በደብዳቤ ቁጥር አምዩ 4/11/34 በቀን 16/02/2010 ዓ.ም ትዕዛዝ ማስተላለፋችንን እየገለጽን ከቀጣዩ ክፍያ አስፈላጊውን የጉዳት ካሳ ተቆርጦ ለዩኒበርሲቲው ገቢ የሚደረግ መሆኑን ማሳወቅ አስፈልጓል፡፡ ለአስረጅነትም ደብዳቤው ተያይዟል

### 3.8.2. <u>በቅድመ ክፍያ ሂሳብ መያዝ ሲገባው ያለአግባብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፤</u>

#### 3.8.2.1. <u>ግኝት</u> ፤

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/2 ፊደል ለ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፤ ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው በቀን 29/07/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0705120 ብር 64,396.29 ከጀመአ እንጨትና ብረታ ብረት ስራ ማህበር በአባያ ካምፓስ ለተገነባው እስታዲዮም የመግቢያ በሮች ለማሰራት በክፍያ ማዘዣ ደብዳቤ ላይ እንዲሁም በድርጅቶቹ የገንዘብ መቀቢያ ደረሰኝ ላይ 30 ፐርሰንት ቅድሚያ ክፊያ የሚል ሆኖ ሳለ ሂሳቡ በቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ መመዝገብ ሲኖርበት በወጪ የሂሳብ መደብ 6244 የተመዘገበ መሆኑን በኦዲት ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

#### 3.8.2.2. <u>ስጋት</u>፤

ዩኒቨርሲቲው ላወጣው ወጪ እቃውን ወይም አገልግሎቱን ለማግኘቱ ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡

3.8.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ዩኒቨርሲቲው የወጪ ሂሳብ በሚመዘግብበት ወቅት ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ለተፈጠረው ስህተት ተገቢውን ማስተካከያ መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.8.2.4. <u>የስራአመራሩ ምላሽ</u>

ይህ የሆነው ማህበራት በአካባቢ ጨረታ /ፐርፎርማ/ ግዥ አሸናፊ ሆነው ሲቀርቡ እንደ ሌሎች የግንባታ ተቋራጮች የባንክ ጋራንቲ ለቅድመ ክፍያ የማያቀርቡ ስለሆነ ክፍያቸው የሚፈፀመው ጫራታውን አሸንፊው ሥራ ሲጀምሩ ያቀረቡት ማቴሪያልና ያከናወኑበት አገልግሎት ተሰልቶ ከ100% ላይ ስንት ያህል መጠን ሥራው እንደደረሰ በመ/ቤቱ ይዞታ ልማት ዳይሬክቶሬት በኩል ተረጋግጦ በቀረበው የተፈፀመ እንጂ በቀጥታ 30% ምንም አቅርቦትና ሥራ ሳያከናውኑ የተፈፀመ አለመሆኑን እንገልፃለን፡፡ ነገር ግን በፋይናንስና በጀት አስተዳደር በኩል የሂሳብ ምዝገባው በቀጥታ በወጪ የሆነው ያስገቡትን ግብአት ታስቦ ቢሆንም አገልግሎቱን ሰጥተው ተገቢው ባለሙያ የደረሰበትን ገልፆና በማስረጃ ተደግፎ እስከሚቀርብ ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ መሆን ያለበትን አስተያየት የተቀበልን ስለሆነ በቀጣይ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የምንፈፅመው መሆኑን እንገልፃለን ፡፡

3.8.3. <u>ተቀናሽ ያልተደረገ የግንባታ ዊዝ ሆልዲንግ (2%) ሂሳብ</u>

3.8.3.1. <u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 53 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24 መሰረት የመንግስት መ/ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች 1.በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 10 ሺ በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ከሚፈጸም ክፍያ እና 2. በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 24 ተ.ቁ 2 ከሀ) እስከ ቸ) ለተዘረዘሩት አገልግሎቶች በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ አገልግሎት ውል ከብር 500.00(አምስት መቶ ብር) በላይ በሚፈጸም ክፍያ ለሚያቀርቡ ግብር ከፋዮች ከሚፈጽሙት ማናቸውም ክፍያ ላይ ሁለት በመቶ (2%) የንግድ ትርፍ ግብር (withholding Tax) ቀንሰው ክፍያ መፈጸም እንዳለባቸው የተደነገገ ቢሆንም በአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በተለያዩ የባንክ ወጪ ማስመስከሪያዎች ከተለያዩ ህንጻ ስራ ተቋራጮች በድምሩ ብር 3,178,253.56 ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ቀሪ ማድረግ

ሲገባው ብር 2,386,805.05 ተቀናሽ በመደረጉ በልዩነት ብር **791,448.51** ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ያልተቀነሰ ዊዝሆልዲንግ ታክስ(2%) መገኘቱ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡ (የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ በአባሪ ቀጥር 14 ተያይዟል)

**3.8.3.2. _ስጋት_**

የማናቸውም ከአገልግሎትም ሆነ ከግዥ መቀነስ ያለበት ግብር ተቀንሶ ወደሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በወቅቱ ገቢ ካልተደረገ መንግስት በግብር ሊሰበስብ የሚችለውን ሂሳብ ላይሰበሰብ ይችላል። እንዲሁም የመንግስት የበጀት አሸፋፈን ስርዓትን ሊጎዳ ይችላል፤፤

**3.8.3.3. _የማሻሻያ ሃሳብ_ ፣**

ዩኒቨርሲቲው ያለአግባብ ሳይመዘገብና ሳይቆረጥ የቀረውን ከተከፋይ ሂሳቦች ላይ ግብርን ቀንሶ ስለማስቀረት በተቀመጠው መሰረት ከድርጅቱ ሰብስቦ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ በማድረግ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

**3.8.3.4. _የስራአመራሩ ምላሽ_**

ይህ የሆነው ሂሳብ ተሰርተው የሚቀርበው በድርጅቱ አማካሪዎች እና በግንባታ ጽ/ቤት የተቀጠሩ ባለሙያዎች በክፍያ ሰርተፍኬት አዘጋጅተው ያቀረቡትን ሂሳብ መሠረት በማድረግ የተፈፀመ ቢሆንም በፋይናንስ በኩል  ክፍያውን ያዘጋጁት አንዳንድ የፋይናንስ ባለሙያዎች ለሥራው አዲስ በመሆናቸው ተዘጋጅተው የተላለፈ ቢሆንም በቀጣይ ከህንፃ ተቋራጮች ጋር በመተማመን ከቀጣይ ክፍያቸው ላይ ቀንሰን ለመንግሥት በማስተላለፍ የምናስተካክል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 4. _የተሰብሳቢ ሂሳብ፣_

### 4.1. _በደንቡ መሠረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣_

**4.1.1. _ግኝት_፣**

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ኦዲት ሲደረግ ፡

- በ4201 የሂሳብ መደብ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መወራረድ ቢኖርበትም

ብር 3,057,477.61 ከ2 ዓመት እስከ 7 ዓመት እና

ብር 7,649,836.50 ከ1 ወር እስከ 2 ዓመት፣ በድምሩ ብር **10,707,314.11** ሳይወራረድ መገኘቱን፤

- 4202 የሂሳብ መደብ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

ኩልፎ ካምፓስ ከፍሬህይወት ታደሰ ብር 47,433.60 እና አባያ ካምፓስ ከከድጃ ሁሴን ብር 67,432.22 በድምሩ ብር 114,865.82 ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የጥሬ ጉድለት የተመዘገበና ሳይወራረድ መገኘቱን፣

- በ4203 የሂሳብ መደብ በ10 የተለያዩ ግለሰቦች ብር **35,178.00** ከ6 እስከ 10 ዓመት ያልተወራረዱ መሆኑን፤
- በ4211 የሂሳብ መደብ

ብር 605,248.33 ከ6 የተለያዩ ግለሰቦች ከ3 እስከ 7 ዓመት መኖሩን እና

ብር 2,067,597.06 ከ1ወር እስከ 1ዓመት በድምሩ ብር **2,672,845.39**

ለተለያዩ ዕቃ ግዥዎች የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ፤

- በ4274 የሂሳብ መደብ በመሳይ ገረመው ስም ብር 132,568.39 ከ2008 ጀምሮ የተመዘገበ እንዲሁም፤
- በ4253 የሂሳብ መደብ ብር 9,345,338.40 ከ1ዓመት እስከ 5ዓመት፤ ለዕቃ አቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ፤

በጠቅላላ በድምሩ ብር **23,008,110.11** በወቅቱ ሳይወራረድ የቆየ ሂሳብ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 4.1.2. <u>ስጋት</u>፣

ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ካልተወራረዱ ከቆይታ ብዛት ወደ ማይሰበሰቡበት ደረጃ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡

### 4.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ውዝፍ ተሰብሳቢ በወቅቱ እንዲወራረድ እና የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ተገቢውን ቁጥጥርና ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

### 4.1.4. <u>የሚመለከተው አካል ምላሽ</u>

ተገቢው እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በኦዲት ግኝቱ መሠረት የሚተገበር መሆኑን እንገልፃለን፡፡

## 5. ተከፋይ ሂሳብ ፣

### 5.2. በወቅቱ ለባለመብቱ ያልተከፈለ ሂሳብን በተመለከተ፣

#### 5.2.1. ግኝት ፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8/5 ፊደል ሀ መሠረት ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ መረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት የተከፋይ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሂሳብ መደብ 5055 ብር 153,366.00 ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ፣ ብር 622,297.12 ከ**2003** ዓ.ም ጀምሮ፣ ብር 5,333.33 ከ**2004** ዓ.ም ጀምሮ፣ ብር 929,615.91 ከ**2007** ዓ.ም ጀምሮ፣ ብር 205,000.00 ከ2008 ጀምሮ በጠቅላላ ድምር ብር 1,915,612.36 የተለያዩ የአቅራቢዎች የመያዣ ሂሳብ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 1001 ብር 262,228.60 ልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች በሚል የተመዘገበ እና የመያዣ ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ መሆኑ እና የተለያዩ የአቅራቢዎች የመያዣ ሂሳብ በሂሳብ መደብ 5055 ሲያዝ ለባለመብቱ በወቅቱ የመያዣ ሂሳቡ ያልተከፈለው አቅራቢዎቹ እቃውን ለዩኒቨርሲቲው ሙሉ ለሙሉ ገቢ ባለመድረጋቸው ወይም የተያዘባቸውን ሂሳብ ባለመጠየቃቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማወቅ ያልተቻለ መሆኑ  ተረጋግጧል፡፡

#### 5.2.2. ስጋት ፣

ሂሳቡ የሚከፈለው  አካል ባለመታወቁ ገንዘቡን ከተከፋይ ሂሳብ ተቀናሽ ለማድረግ አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሂሳቡ በተገቢው ማስረጃ ተለይቶ ባለመያዙና በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ባለመመዝገቡ የሂሳብ ሪፖርቱን ያዛባዋል፡፡

#### 5.2.3. የማሻሻያ ሃሳብ ፣

ከአቅራቢዎች ላይ በመያዣ የተያዘው ሂሳብ በወቅቱ ለአቅራቢዎቹ ያልተከፈለው አቅራቢዎቹ እቃውን ለዩኒቨርሲቲው ሙሉ ለሙሉ ገቢ ባለመድረጋቸው ወይም የተያዘባቸውን ሂሳብ  ባለመጠየቃቸው መሆኑን  እና ዩኒቨርሲቲው በመለያ ቁጥሮች ተለይተው የተመዘገቡትን ተከፋይ ሂሳቦች ለየትኛው አካል እንደሚከፈሉ በማጥራት እና ተገቢውን ማስረጃ በማሰባሰብ ገንዘቡን ለሚመለከተው አካል እንዲከፈል እና

ከተከፋይ ሂሳብ እንዲቀነስ ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የመያዣ ሂሳቡ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መያዝ ይኖርበታል፡፡

5.2.4. <u>የሚመለከተው አካል ምላሽ</u>

<u>በፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክተር የተሰጠ ምላሽ</u>

ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ የተሰጠው አስተያየት ተገቢ ስለሆነ በቀጣይ የሚሠራ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

5.3. <u>ገንዘቡ የሚከፈለው ድርጅት ወይም ግለሰብ ሳይገለፅ በተከፋይ ተቀጽላ ሌጀር ላይ ያለን ሂሳብ በተመለከተ</u>፣

5.3.1. <u>ግኝት</u> ፣

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም አንቀጽ 8/5/ሀ ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት እንዲሁም መ) ለእያንዳንዱ የተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት ክትትል ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በሂሳብ መደብ 5054/ሌሎች የሚያዥያ ሂሳቦች/ በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 0001 ብር 300,751.16 ልዩ ልዩ ከመደበኛ ሂሳብ ተከፋይ እንዲሁም ብር 18,185,592.49 ልዩ ልዩ ከውስጥ ሂሳብ ተከፋይ በሚል በድምሩ ብር 18,486,343.65፣ ለማን እንደሚከፍል በዝርዝር የማይታወቅና የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ሠነድ ያልቀረበ በመሆኑ ሂሳቡን ለማጣራት ያልተቻለ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

5.3.2. <u>ስጋት</u>፣

የሂሳብ ሪፖርቶች በሠነድ ማስረጃ ካልተደገፉ ተዓማኒነት ላይኖራቸው ይችላል፡፡ተከፋይ ዕዳዎች በወቅቱ ካልተከፈሉ በቆይታ ብዛት ከፍተኛ የዕዳ ክምችት ሊኖር ስለሚችል ተቋሙን ለጉዳት ሊዳርግ ይችላል፡፡

5.3.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

ተከፋይ ሂሳቦች በሰነድ ማስረጃ እንዲደገፉ፣ የሠነድ ማስረጃ የሌላቸው ተከፋይ ሂሳቦች በማጣራት ማስተካከያ እንዲሠራለት እንዲሁም የዕዳ ክምችት እንዳይኖር ተከፋይ ሂሳቦች ለማን እንደሚከፈሉ በማጣራትየእርምት እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

### 5.3.4. የሚመለከተው አካል ምላሽ

ተከፋይ ሂሳቦችን በተመለከተ እያንዳንዱ በ Subisdvry ledger የተለዩ ቢሆንም መረጃ ያላቸው ተሰብሳቢዎችን ማደራጀት-መረጃ የሌላቸውን በሂሳብ ማስተካከያ በመግለፅና የእርምት እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

# 6. በጀት

## 6.1. ግኝት፣

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6/2 መሠረት የበጀት ዝውውር ወይም ተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር ለአንድ የመንግስት መ/ቤት በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈፀም እንደማይቻል ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር፣አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተመደበው የወጪ ሂሳብ በበጀት አጠቃቀም ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፡

- ለመደበኛ በጀት ከተደለደለው ውስጥ ለምግብ አገልግሎት ብር 9,014,538.64 ከበጀት በላይ ስራ ላይ የዋለ መሆኑ ፣በሌላ በኩል ደግሞ ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ብር 1,489,305.86 ፣እቃና አገልግሎቶች ብር 2,886,969.01፣ ለጉዞና መስተንግዶ አገልግሎቶች ብር 811,216.90፣ለእድሳትና ጥገና አገልግሎቶች ብር 2,722,312.59፣በውል ለሚፈፀሙ የአገልግሎት ግዥዎች ብር 4,253,895.27፣ ለስልጠና አገልግሎቶች ብር 933,491.64 እና ለግለሰቦች እርዳታና ስጦት ብር 798,634.00 በድምሩ ብር 13,895,825.27 በፐርሰንት 21.59% ተራፊ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡
- ለካፒታል በጀት ከተደለደለው ውስጥ ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ብር 190,840.68 ፣ እና ለመኖሪያ ያልሆኑ ህንጻዎች ግንባታ ብር 196,497,640.23 (ሲቀነስ ብር 125,851,672.07 በበጀት ዓመቱ በቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ) ብር 70,645,968.16 በድምሩ ብር 70,836,808.84 በፐርሰንት 39.35% ተራፊ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡
- ከውስጥ ገቢ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ ሰብዓዊ ለሆኑ አገልግሎቶች ብር 4,509,880.92 ፣ለእቃና አገልግሎቶች ብር 4,161,184.97 ፣ ለጉዞና መስተንግዶ

አገልግሎቶች ብር 3,404,460.78 ፣ለእድሳትና ጥገና አገልግሎቶች ብር 645,981.00 ፣በውል ለሚፈፀሙ የአገልግሎት ግዥዎች ብር 659,918.05 ፣ለስልጠና አገልግሎቶች ብር 221,700.00 ፣ለቋሚ ንብረቶች መግዣ ብር 2,619,300.00 እና ለተቋሞችና ድርጅቶች እርዳታ፣መዋጮና ድጎማ ብር 960,000.00 በድምሩ ብር 17,182,425.72 በፐርሰንት 48.77% ተራፊ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር ሁኔታ (በአባሪ ቁጥር 16 ቀርቧል )

6.2. <u>ስጋት</u> ፣

እንዲሁም የወጪ በጀቱ በእቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

6.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u> ፣

የዩኒቨርሲቲው ዕቅድና ክንውን የተጣጣመ እንዲሆን መደረግ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

6.4. <u>የሚመለከተው አካል ምላሽ</u>

<u>በፋይናንስና በጀት አስተዳደር ዳይሬክተር የተሰጠ ምላሽ</u>

የተማሪዎች ምግብ በጀት ኮድ 6216 በአብዛኛው በአቅራቢያዎች የጫራታ ሁኔታን መሠረት ያደረገና የወቅቱን የምግብ ጥሬ-ዕቃዎች ዋጋ መጨመርን ምክንያት የተከሰተ ስለሆነ በበጀት ኮዱ ላይ ዝውውር ማድረግን ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ሚ/ር የማይቀበልና ሪፓርቱንም በደረሰበት የወጪ አፈፃፀም የሚቀበል በመሆኑ ነው፡፡ የመደበኛ በጀት ኮዶች ላይ የበጀት ዕጥረት እያለ በአንዳንድ ኮዶች ላይ የበጀት መትረፍ የሚታይ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው የበጀት ዲስንተራላይዘሽን ለየካምፓሶች በመሰጠቱ ምክንያት ከካምፓስ ወደ ካምፓስ የበጀት አጠቃቀምን ማዛወር ባለመቻሉ የተከሰተ ሲሆን በቀጣይ ተራፊ በጀቶችን ከካምፓሶች ወደ ማዕከል በማዛወር የምንጠቀም መሆኑን እንገልፃለን፡፡ እንዲሁም የካፒታል በጀትና የውስጥ ገቢ በጀት አፈጻጸም ላይ በቀጣይ ማስተካከያ የምናደርግ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

# 7. ንብረት ፤

## 7.1. የንብረት አመዘጋገብ፣አያያዝ እና አጠባበቅ በተመለከተ፣

### 7.1.1. ግኝት፣

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ንዑስ 5 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በእጃቸው ያለውን የመንግሥት ንብረት በጥንቃቄ የመያዝ፤የመጠቀም፤ የመቆጣጠር እና አገልግሎቱ ሲያበቃ ወይም አገልግሎቱ ላይ በማይውሉበት ጊዜ በወቅቱ በተገቢው መንገድ እንዲወገዱ የሚል ሲሆን በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

በዋና ግቢ አላቂ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

- ብዛት ያላቸው መወገድ ያለባቸው የተለያዩ ዕቃዎች ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ኮምፒዩተር ግላሶች ፣ የፎቶ ኮፒ ቶነሮች ፣ የኮንቴንስ ወረቀቶች ፍሎፒ ዲስክ ሆንደር እንዲሁም የርቀት ትምህርት የማስተማሪያ መጽሐፍት መሳሰሉት ለበርካታ አመታት ሳይወገዱ በስቶር ውስጥ ከአዳዲስ አላቂ እቃዎች ጋር በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ዋና ግቢ ቋሚ እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣
- ቢንካርዶች ከንብረቶቹ ጋር ተያይዞ የማይገኝና ወቅታዊ ምዝገባ ሳይደረግ ለብዙ ቀናት የሚቆዩ መሆኑን፤
- የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያየ ብራንድ ያላቸው ቴሌቪዥኖች፣ የፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ስታብላይዘር፣ ወንበሮች፣ ፍሪጆች፣ ፋክስ ማሽኖች፣ ስቶቮች፣ ፕሪንተሮች፣ ኮምፒዩተሮች እና UPS ምንም የሚወገዱ በሚል የተያዙ ቢሆንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድባቸው ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፣
- በ2009 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረት ቆጠራ ቢደረግም ቆጠራው የተደረገው በንብረት ክፍል ውስጥ ያሉትን ቋሚ እቃዎች ብቻ እንጂ በሰራተኞች እጅ ያለው እቃ ያልተቆጠረ መሆኑ፣

የኮንስትራክሽን እቃዎች የንብረት አያያዝን በተመለከተ፣

- ከተገዙ ብዙ ጊዜ የሆናቸውየሻወር /የመታጠቢያ/ ቤት ሳህኖች ዩኒቨርስቲው ከሚያስገነባቸው ህንጻዎች ጋር የማይገጥሙ በመሆናቸው በሚል ያለመፍትሄ ተከማችተው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

- ቴብል ፋን (የጠረጴዛ ቬንቲሌተር) ካርቶን አዳዲስና አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸውን ለመቁጠር ያልተቻለ ለብዙ ጊዜ የቆየ ምቹ ባልሆነና ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ የተቀመጡ መኖሩን፣ እንዲሁም ቶርኖ እና ከ1980 ጀምሮ ገባ የተባለ የውሃ ማሞቂያ ቦይለር በቁጥር 9 በመጋዘን ውስጥ አለአግባብ የሚገኙ መሆኑን፤
- በሞዴል ወጪ ተደርገዋል በሚል ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ የሌላቸው የዕቃ ማጠቢያ ሽቦ፣ የቀለም መቀቢያ ብሩሽ በካርቶን(5*120) 600, የቢሮ ቁልፍ ሙሉ ሲሊንደር ብዛት 250፣ ቆርቆሮዎች ብዛት 268፣ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና ሌሎችም ይገኛሉ

<u>የተሽከርካሪዎች መለዋወጫ እቃዎች አያያዝን በተመለከተ</u>

- በመኪና መለዋወጫ ስቶር ውስጥ አዲስና አሮጌ እቃዎች አብረ ውመቀመጣቸው፣
- በመጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ የመኪና መለዋወጫ ያልሆኑ ለረጅም ዓመታት የቆዩ ስማቸው የማይታወቅ እንደታሸጉ የተቀመጡ ብዛት 12 ማሽኖች፣ ዱፕሊኬቲንግ 23 ካርቶን፣ ዋይት ስቴንሲልስ እና ሌሎች እንዲሁም ጎማዎች ያለአገልግሎት መቀመጣቸው፣
- የተለያዩ ዓይነት የመኪና ባትሪ ባንድ ቢን ካርድ የተመዘገበ መሆኑን

<u>በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት አላቂ ዕቃዎችን በሚመለከት</u>

- በሞዴል ወጪ ተደርገው በመጋዘን የሚገኙ ወረቀት በደስጣ 390,
- ማሽኖቻቸው የሌለ አገልግሎት የማይሰጡ ቀለሞች ብዛት ናኖዳስ 410 ቀለም,

<u>የቋሚ ዕቃዎችን በሚመለከት</u>

- በሞዴል ወጪ ተደርገው በመጋዘን የሚገኙ ሜጋ ቀለም 28 ጋሎን መኖሩን፣
- በንብረት መጋዘን ውስጥ ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ወተር ቴክኖሎጂ ዲፓርትመንት ለፊልድ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ታጣፊ ድንኳኖች እና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ዕቀዎች ለረጅም ዓመታት በመጋዘን ውስጥ እንደሚገኙ፣
- ቬንትሌተር (Desk Fam) አገልግሎት የሚሰጡ ቢንካርድ የሌላቸው ብዛት 38 ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን፣
- የተበላሹ ሜጋ ቀለሞች ብዛት 30 የሚገኙ መሆኑን፣
- ቢንካርድ ወቅታዊ የማድረግ ችግር መኖሩን

በኩልፎ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ

- ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፣
- ንብረቶች ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ በተዘበራረቀ ሁኔታ ለአቀማመጥ ምቹ ባልሆነበትና አቧራማ በሆነበት ሁኔታ ንብረቶች ተቀምጠው መገኘታቸው
- የተለያዩ ዕቃዎች ቢንካርዶች ወቅታዊ ምዝገባ አልተደረገባቸውም
- ፕሮጀክተሮች፣ ጀኔሬተር፣ የጤረጴዛ ቬንትሌተር፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ የፕሪንተር ቀለሞች ኮምፒተሮች፣ ፎቶ ኮፒ፣ የማባዣ ቀለሞች እና ሌሎችም ተመላሽ የተደረጉ አሮጌ ዕቃዎች አገልግሎት ከሚሰጡ ንብረቶች ጋር አንድ ላይ መቀመጣቸው፡፡

ነጭ ሣር ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ

- አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፣
- ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቆጠራ በፊት ንብረቶቹ በፊሰስ ሪፖርት ላለማቅረብ ንብረቱ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ወጪ የተደረጉ የጽዳት ዕቃዎች(መወልወያ ብዛት 380, የልብስ ሳሙና 2,683, ቪም 1475, ከፍተኛ ቁጥር ያለው የተለያዩ ዓይነት የፕላስቲክ መጥረጊያና የዘንባባ መጥረጊያ) የኮንስትራክሽን ዕቃዎች(ሚስማር የተለያየ ሳይዝ በካርቶን 100, ሰርኩዩት ብሬከር ብዛት 22 በካርቶን፣ ፊውስ ብዛት በካርቶን 97, እና የፕሪንተር ወረቀቶች በደስጣ 1334) በሞዴል ወጪ እንዲያደርጉ ተደርጎ በቢንካርድ ላይ ወጪ ወይም ባዶ በማድረግ ንብረትን ለቁጥጥርና ለብክነት በሚዳርግ መልኩ የሚገኙ መሆኑን፡፡
- በመጋዘኑ ውስጥ ከቃጠሎ የተረፉ አገልግሎት የሚሰጡ HP A.L steincel printer፣ HOT Air Oven , የማብሰያ ዕቃዎች፣ የህክምና የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ ቴሌቪዥን፣ ዲኮደር፣ የማስተማሪ ዕቃዎች፣ እንዲሁም አሮጌ መጋዘን ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ መሆኑን እና በአቧራና በአቀማመጥ ለብልሽት ሊዳረግ በሚችልበት ሁኔታ የሚገኝ መሆኑን
- የተለያዩ አገልግሎት ሰጥተው ተመላሽ የተደረጉ ኮምፒውተሮች፣ ላፕቶፖች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ በንበሮች፣ የፕሪንተር ቀለሞችና የመሳሰሉት በመጋዘን ውስጥ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ መገኘታቸው

በጫሞ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ

- ቋሚ፣ አላቂና ያገለገሉ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን እንደሚገኙ፣
- ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቆጠራ በፊት ንብረቱ በመጋዘን ውስጥ እያለ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች የተለያዩ ዓይነት የኮንስትራክሽን፣ የቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ እና የጽዳት ዕቃዎች ከነዚህም ውስጥ የመንገድ ላይ መብራቶች(Street lighting luminaire) ብዛት 30, የኤሌክትሪክ ሽቦ 2.5ሚ.ሚ ባለ100 ሜትር ብዛት 21, ኤሌክትሪክል ቱል ኪት እሽግ ብዛት 8, ፍሎረሰንት ኦልደር 36እና ባለ18 ዋት ብዛት 125, ድሪል ማሽን ጅክሰን ማሽን ብዛት 5, ዊልዲንግ ማሽን ብዛት 1, ቬንትሌትር ብዛት 10, የጋውን ጨርቅ በሜትር 794, ሳይፎን ፍሌክሰቢል 833, የተለያየ ሳይዝ ወረቀት ብዛት ያለው፣ ኤር ፍሬሽነር 3,355, የሽንት ቤት መርዝ 1,288, ሮች ኪለር 2,137, የኤሌክትሪክ ኬብል 120ሜ, ድል ቀለም ብዛት 276, የሆቴል ማናጅመንት ብዛታቸው የማይታወቅ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች, ፕሪንተሮች 22, ኤልሲዲ 6, የቆሻሻ ማስቀመጫ ባልዲ ብዛት 50 እና የተለያዩ ዕቃዎች በሞዴል ወጪ እንዲያደርጉ ተደርጎ በቢንካርድ እና በስቶክ ካርድ ላይ ወጪ ወይም ባዶ በማድረግ ንብረትን ለቁጥጥርና ለብክነት በሚዳርግ መልኩ በፎርም የሚወጣ በሚል በንብረት መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፡፡
- የተለያዩ ተመላሽ የተደረጉ ላፕቶፖች, ፕሮጀክተሮች እና ሌሎች ዕቃዎች በመጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑን፡፡

በአባያ ካምፓስ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች አያያዝን በተመለከተ

- መወገድ ያለባቸው የተበላሸ ብዛት ከ100 ኩንታል በላይ ጤፍ ከቋሚና አላቂ ዕቃዎች ጋር በመጋዘን ውስጥ የሚገኝ እንዲሁም ሌሎች ተመላሽ የተደረጉ፣ ያገለገሉ ወንበሮች ፣ የመምህራን አልጋዎች ባለ 1.20ሜ ብዛት 112፣ ችፑድ 1.50ሜ ብዛት የማይታወቅ፣ ኮምፒውተሮች፣ ቤድ ሳይድ ካቢኔት ብዛት 430, ፎቶ ኮፒ, ላፕቶፖች, ፕሮጀክተሮች, ቴብል ያልተገጠመ ድሮዎር፣
- እንዲሁም ቢንካርድ ሆነ ስቶክ ካርድ የሌለው የቧንቧ ዕቃዎች ብዛት ያላቸው፣ የጠረጴዛ ተገጣሚ ዕቃዎች ስፒከር እና ስፒከር ስታንድ ሞንታርቦ፣ Galileo scope ብዛት 3 በ2006 በእርዳታ ገባ የተባለ፣ free standing cooker አዲስ ቢሆንም አይሰራም የተባለ መኖሩን፣

- ብዛት ያላቸው የቢሮ ዕቃዎች በሙሉ በሞ/22 ወጪ ያደረጋቸው መሆኑን ንብረቶች በመጋዘን ውስጥ ተከማችተው እያሉ ከሰኔ 30 ቀጠራ በፊት ንብረቱ ለተለያዩ የስራ ክፍሎች ወጪ ተደርጓል ይህም የተለያዩ ዓይነት የኮንስትራክሽን፣ የቧንቧ፣ የኤሌክትሪክ እና የጽዳት ዕቃዎች ከነዚህም ውስጥ ሻወር ጌት ቫልቭ የተለያየ ሳይዝ ብዛት 190, Upvc የተለያየ ሳይዝ ብዛት 85, ሲሚንቶ ብዛት 100 ኩንታል, ቱቦላሬ ብዛት 550, (ሮች ኪለር ብዛት 1,980., ኤርፍሬሽነር 721, ሶላር ሳሙና 903, አጃክስ 1095, ኦሞ 530, የእጅ ጓንት ብዛት 40, እስፖንጅ 891, መወልወያ 1304, የፕላስቲክ መጥረጊያ 1016, ጋውን 600ሜ, ፎቶ ኮፒ ወረቀት 3850, ማበዣ ወረቀት 1000, ኡሁ 1670,) የሚገኝ መሆኑን፣

